## መግቢያ

የአየር ሁኔታና ጠባይ ክስተቶች የማይነኩት የኢኮኖሚ ዘርፍ እንደሌለ ይታወቃል፡፡ የሚቲዎሮሎጂን አገልግሎት በማሻሻል የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ለማርካት የሚካሄደዉ ጥረትም እንደዚሁ ከብዙ አቅጣጫ ሊመዘን የሚገባዉ ጉዳይ ይሆናል፡፡

የብሄራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 201/73 ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ያሳየዉ እድገት በቀላሉ የሚገመት ባይሆንም በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ ያለዉን ብቃት ከደንበኞች የመረጃ ፍላጎት አንጻር ስንመለከት ገና ብዙ መስራት እንደሚገባዉ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ለአገሪቱ የልማት እንቅስቃሴዎች በብቃት ለማዋልና ንብረትና ህይወትን ከአደጋ ለመከላከል እንዲቻል የኤጀንሲው (የ2003- 2007) ስትራቴጂክ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

የዕቅዱ ዋና መነሻም መንግስት ለአጭርና ለረጅም ጊዜ የነደፋቸዉን የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕቅዶችን ለመተግበር እንዲሁም የእድገትና የትራንስፎርሜሽ ዕቅድ ስኬትን ለማምጣት ለሚደረገው ርብርብ የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማበርከት እና ኤጀንሲዉ የአገልግሎት አሰጣጡን የበለጠ በማሻሻል በልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች የሚገኙ የኤጀንሲዉ ሠራተኞች ደንበኞች ባለድርሻዎችና ተባባሪዎች ተሳታፊ የሆኑበት የመረጃ ፍላጎትን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመመለስ የሚያስችል ስልት ለመንደፍ ነዉ፡፡

(የ2003- 2007) ስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅት ለማከናወን ቀደም ሲል ከ2000-2004 የታቀደዉና የተተገበረዉን የኤጀንሲዉን ስትራቴጂክ ዕቅድ በስፋትና በጥልቀት ተገምግሟል፡፡ ላለፉት ሶስት ዓመታት በስትራቴጂክ ዕቅድ ከተያዙት የስራ ዘርፎች መካከል አብዛኛው የተከናወነ ሲሆን አንዳንድ ስራዎች ደግሞ ከዕቅድ ዉጭ ተከናዉነዋል፡፡ በመሆኑም

ኤጀንሲዉ ከቀዳሚዉ ስትራቴጂክ ዕቅድ የቀሩትንና በቀጣዮቹ ጊዜያት በኤጀንሲዉ መከናወን በሚገባቸዉ መሰረተ ጉዳዮች ላይ እና የእድገትና የትራንስፎርሜሽ ዕቅዱን ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ የኤጀንሲዉ ዉጫዊና ዉስጣዊ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን በመቃኘት በተግባር እንቅስቃሴ ወቅት ሊኖሩት የሚችሉት አመቺ እና/ወይም አመቺ ያልሆኑ ሁኔታዎች እንዲሁም ያሉት ጠንካራና ደካማ ጎኖች ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡ በዚሁ መሰረት በዉጫዊ ቅኝትና በዉስጣዊ ግምገማዉ ዉጤት መሰረት የኤጀንሲዉን ተልዕኮ ለመወጣት ያስችላል ተብሎ የታመነበት የኤጀንሲዉ (የ2003-2007) ስትራቴጂክ ዕቅድ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

## 1. አለም አቀፋዊና አገራዊ ሁኔታዎች

## 1.1 አለም አቀፋዊ ሁኔታ

በሚቲዎሮሎጂ መስክ ያለው አለም አቀፍ ትብብር ወደ 137 አመታት አካባቢ እንደሚጠጋ የአለም ሚቲዎሮሎጂ ታሪክ ያመለክታል፡፡ ለዚህም ዋነኛ መንስኤ የአየር ጠባይ በአገሮች ድንበር የሚወሰን ሳይሆን፣ የራሱ የሆነ የተፈጥሮ ሕግጋት ስላሉትና ባንዱ አካባቢ የደረሰው የአየር ሁኔታ ጠባይና በሌላ አካባቢ ካሉት የከባቢ አየር ክስተቶች ጋር የተዛመደ በመሆኑ፣ በመረጃ ልውውጥ እንዲሁም ብዙ አገሮችን ሊነኩ የሚችሉ የአካባቢ አየር ክስተቶችን ለመከታተል አለም አቀፋዊ ትብብር አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡

ይህ አለም አቀፍ ግንኙነት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገሮች መካከል ያለውን ትብብር እያጠናከረው እንደመሄዱ መጠን በተለይ የአየር ሁኔታና ጠባይ የማይነኩት የኢኮኖሚ ዘርፍ የሌለ በመሆኑ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አሳሳቢ እየሆኑ በመጡት የአየር ጠባይ ለውጥ፣ የድርቅና የጎርፍ፣ የኦዞን መሳሳት ወዘተ ክስተቶች በአጠቃላይ በአየር ሁኔታ መዛባት ሳቢያ ያለው ትብብር በመረጃ ልውውጥና የአየር ጠባይ ክስተቶችን በመከታተል ሳይገደብ፣ ጥናትና ምርምር ሥራዎችም አለም አቀፋዊ ትብብርን የበለጠ የሚሹ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በተለይም በዓለማችን በአሁኑ ሰዓት ከአየር ጠባይ መዛባት (Climate Variability) ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ እንደ ሀሪኪን ትሮፒካል ሳይክሎን (Tropical Cyclone) ፣ የመሬት መደርመስ ፣ በዋልታዎች የሚገኘው ግግር በረዶ እየቀለጠ መሄድ የመሳሰሉት ክስተቶች አለምአቀፋዊ ትኩረት እየሳቡ መጥተዋል፡፡

የምድር ከባቢ አየር የቅኝት መርሀ ግብር (World Weather Watch Programme) ፣ የአለም ከባቢ አየር የምርምር መርሀ ግብር (Global Atmospheric Research Programme) የተባበሩት መንግስታት የአየር ጠባይ ለውጥ ስምምነት ማዕቀፍ (United Nations Frame Work Convention on Climate Change, UNFCCC) ፣ በአገሮች መካከል ሊኖር የሚችለውን የቴክኖሎጂ ሽግግር በማጠናከር በኩል በአብነት ሊጠቀሱ የሚችሉ አለም አቀፍ የትብብር ውጤቶች ናቸው፡፡

እንዲህ አይነቱ አለም አቀፍዊ ትብብር ባንድ ጎኑ በሚቲዎሮሎጂ መስክ አይነተኛ ባህሪ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ እያደገና እየጎለበተ በከፍተኛ ፍጥነት

እየተለዋወጠ በሚሄደው የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስና የቴክኖሎጂ ውህደት አንፃር እያንዳንዱ ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ድርጅት ራሱን አጠናክሮ መገኘት አለበት፡፡ እንዲሁም ለአህጉራዊና ክፍለ አህጉራዊ የምርምር፣ የአየር ትንበያና የስልጠና ማዕከል በመሆን በሚገኘው የቴክኖሎጂ ሽግግር በአገሪቱ ለሚገኙ ተገልጋዮች የተሻለና የተጠናከረ አገልግሎት ለማበርከት መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል፡፡

የአለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት አባል የሆኑ ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ እና ሀይድሮሎጂ ድርጅቶች በየአገሮቻቸው ዕድገትና ልማት ላይ ስላላቸው ሚና፣ ለብሔራዊና አገራዊ ጉዳዮችና ስለሚያደርጉት አስተዋፅኦ እንዲሁም ስለሚመለከታቸው ዋንኛ ጉዳዮች መረጃን ማሰባሰብ የሚያስችል መጠይቅ ለአባል አገራት በአለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት ተበትነው ከተሰባሰቡት መጠይቆች አብዛኞቹ ብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ድርጅቶች እንደ ዋነኛ አስተዋፅኦ ያስቀመጡት የሕይወትና ንብረት ደህንነትን ከልዩ ልዩ ጎጂ የአየር ጠባይ ሁኔታዎች በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አማካይነት መጠበቅ በተፈጥሮ አደጋዎች ሳቢያ ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችን መቀነስ፣ ለዘላቂ ልማት (Sutainable development) አስፈላጊ የሆኑ ግልጋሎቶችን ማቅረብ እንደ ዋነኛ ብሔራዊ ተዋፅኦ ሲመለከቱት ከዋነኛ ግልጋሎቶችም አንፃር ለአየር ትራንስፖርት የተፈጥሮ አደጋ ጉዳት ለመከላከልና የግብርና ምርትን ለማሳደግ ለአካባቢ ጥበቃና ለመገናኛ ብዙሐን አስፈላጊ የተጠናቀሩና የተተነተኑ መረጃዎች ማቅረብ ዋነኞቹ እንደሆኑ ያመለክታሉ፡፡

በአብዛኛዎቹ የሚቲዎሮሎጂ ድርጅቶች በዋናነት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ሆነው የቀረቡት ዘመናዊ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎች ተግባራዊ ማድረግ (Modernization) ፣ አቅም ግንባታ ፣ እያደገ ለመጣው የአየር ትራንስፖርት ደህንነት (Aeronautical Meteorology) አስተማማኝ መረጃ የማዘጋጀት እንዲሁም በአገራዊ ዕይታ የሚቲዎሮሎጂ ድርጅቶች ሚና ምን መሆን እንደሚገባው የሚያተኩሩ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ በአለም አቀፍ ደረጃ የሚንፀባረቁት ሁኔታዎች ይህን ሲመስሉ በአገሮች መካከል ካሉ ኢኮኖሚያዊና የልማት ዕድገት ልዩነት አንፃር በየአገሮቹ ያሉ የሚቲዎሮሎጂ ድርጅቶች አጠቃላይ ሚና እንደየ አገሮቹ ተጨባጭ ሁኔታ ሊለያይ እንደሚችል ግንዛቤ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የአየር ሁኔታና ጠባይ (Weather & Climate) ድንበር የማያግዳቸው ክስተቶች በመሆናቸው ጎጂ የሆኑ የአየር ሁኔታ ገፅታዎችን በሚመለከት ከወዲሁ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ለማዘጋጀትና ለማሰራጨት ዕለት ተዕለት የመረጃ ልውውጥ በአገሮች መካከል ማካሄዱ አስፈላጊ ነዉ፡፡ ይህ አይነቱን የመረጃ ልውውጥ ውጤታማ ለማድረግ አለም አቀፍ የመገናኛ አውታር በአለም አቀፍ የአካባቢ ማዕከላትና (Regional center) ኢንተርኔት መስመር ጋር ግንኙነት በማድረግ መረጃዎችን በስፋት ለመለዋወጥ ይቻላል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣውን የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስና እየረቀቀ የመጣውን አኃዛዊ ትንበያ (Numerical weather prediction, NWP) ደረጃ ለማመልከት እንደ NWP ኮምፒዩተር የመጠቀም አቅምም ባይኖረን እንኳን ከሱፐር ኮምፒዩተሮች የተገኙ ዉጤቶችን እና ለአካባቢያችን ብቻ Numerical Weather Prediction ሞዴሎችን በመደበኛ ኮምፒዩተር በመጠቀም ኤጀንሲዉ ሙከራ በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

## 1.2 ሀገራዊ ሁኔታ

በአገራችን በተለያዩ አመታት በተከሰቱት የአየር ሁኔታና ጠባይ መዛባት ምክንያት ተፈጥረው የነበሩት እንደ ድርቅ ረሃብ እና ጎርፍ የመሳሰሉት ክስተቶች ለህዝቦች ስደትና ለፖለቲካዊ ለውጥ ከፍተኛ ሚና ነበራቸው፡፡ የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በአዋጅ በተሰጠው ሃላፊነት መሠረት እነኝህን አደጋዎች አስቀድሞ በመተንበይ የአደጋዎቹን ጉዳት በመቀነስ እና ህብረተሰቡ የቅድሚያ ጥንቃቄ እንዲያደርግ፣ የትንበያ እና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መግለጫዎች ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ በዚህ መሰረት በአለፍት ዓመታት በሀገራችን የተከሰቱትን የድርቅ እና የጎርፍ ክስተቶችን አስቀድሞ በመተንበይ ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት እና ለህብረተሰቡ በመስጠት ተከስቶ የነበረውን ድንገተኛ አደጋዎቸ ለመቀነስ ተችሏል፡፡

የአየር ሁኔታና ጠባይ ክስተቶች ከቦታ ቦታ ይለያያሉ፡፡ በዚህም መሰረት ከሌሎች የአለም ክፍሎች ይልቅ በሀሩር ክልል (በትሮፒካል ክልል) በሚገኙ አገሮች ላይ የደረቅና የዝናብ ወቅቶች መፈራረቅ በጎላ መልኩ የሚታይ ሲሆን ከወቅት ወቅት

ወይም ከዓመት ዓመት የሚታየው የአየር ጠባይ መዛባት ተደጋጋሚነቱ እየጨመረ ይገኛል፡፡ ኢትዮጵያም በሐሩር ክልል ውስጥ ከሚገኙት ሀገሮች አንዱ በመሆኗ ከፍተኛ የአየር ጠባይ መዛባት ክስተቶች ይታዩባታል፡፡ የድርቅ ክስተት መደጋገም፣ የአፈር መሸርሸር፣ የዘመናዊ የእርሻ ስራዎች አለመስፋፋት ለረሀብ አደጋዎች መደጋገም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

ለዚህም የቅድሚያ ማስጠንቀቂያዎች፣ የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንተናና ትንበያ በመስጠት የድርቅና የጎርፍ አደጋዎችን በመቀነስ ለተለያዩ ሶሽዮኢኮኖሚያዊ ስራዎችና ለህብረተሰቡ ደህንነት ከፍተኛ እገዛ በሚያደርግ መልኩ አስተማማኝና ወቅታዊ መሆን ይኖርበታል፡፡ መንግስት በነደፋቸው የልማት ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎች ፕሮግራሞች ተፈጻሚነት ባለፉት አምስት ዓመታት ኢኮኖሚው በአማካይ በአመት 11 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ ይህ ዕድገት በሀገራችን ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ብቻ ሳይሆን በሌሎች በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ ሀገሮችም ያልታየ ነው፡፡ የመንግስት ፖሊሲና የወደፊት አቅጣጫ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ (2003-2007) ማሳካትና የዕድገቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ኤጀንሲው የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት ይጠበቅበተታል፡፡

ኤጀንሲው የሚሰጣቸው አገልግሎቶች መንግስት ለሚያካሂዳቸው የልማት አቅጣጫን ስኬታማ በማድረግ በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ስለታመነበት በየክልሉ የሚቲዎሮሎጂ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በማቋቋም መረጃዎች ለአካባቢው ህብረተሰብ በማሠራጨት ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ ጋር በመያያዝ ኤጀንሲው የድረገፅ ሥራ በመጀመር በመስመሩ የ24 ሰዓት የሶስት ቀኖች የአስር ቀኖች የወራትና የወቅቶች ትንቢያዎች ጊዜያቸውን ጠብቀው መረጃዎች በመለቀቅ ላይ ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረት በቀን አራት ጊዜ ስለአየር ሁኔታ መረጃ የሚሰጥ 4 የሳተላይት ምስሎች እና የቱሪስት መስህብ ያላቸው የዋና ዋና ከተሞች የአጭር ጊዜ የአየር ሁኔታ ትንበያዎች በ4 ቋንቋዎች በማሰራጨት ላይ ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ ኤጀንሲዉ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ሥራዎች የበኩሉን አስተዋፅኦ የሚያበረክትባቸው በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የተለዩ መስኮች፡-

- ለግብርና ልማት ዘርፍ ስኬታማነት የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት Respons Farming መሰረት ያደረገ የGras Root Meteorological Service (GRMS) አገልግሎትን መስጠት
- ለዉሀና ኢነርጅ ተኮር የHydro meteorology ትንበያና የምክር አገልግሎት መስጠት፣
- ለወባ ለማጅራት ገትርና የአተት ወረርሽኝን ቀድሞ ለመከላከል የሚያስችል የጤና ሚቲዎሮሎጂ ትንበያና የምክር አገልግሎትን ተግባራዊ ማድረግ ፣
- ለግንባታው ዘርፍ የሚቲዎሮሎጂ መረጃን መጠቀም ለግንባታ ሥራ ውጤታማነት ላይ እሴት ይጨምራል፣
- የአቪየሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ዘመኑ በሚጠይቃቸዉ የቴክኖሎጂ አሰራሮች መሰረት ያደረገ ለዉጥን መተግበር
- የአየር ሁኔታ ገፅታዎችን በማጥናት የሚያስከትሉ ተፅዕኖዎችን በቅድሚያ ለመተንበይ የሚያስችል ሳይንሳዊ መሠረት ያላቸው የትንበያ ዘዴዎች /Prediction techniques/ በመገንባትና በመጠቀም በአገሪቱ ሊከሰት የሚችለውን የአየር ጠባይ መዛባትንና ለውጥን እንዲሁም በተፈጥሮ ሀብት /Environmental Resources/ ላይ ሊደርስ የሚችለውን የአየር ብክለትና ሌሎች ጎጂ ክስተቶችን በቅድሚያ መረዳት ማስቻል፣
- የአገሪቱን መልከአምድራዊ ገፅታዎች የሚወክሉትን የአየር ሁኔታ መረጃ መመዝገቢያ ጣቢያዎች በማቋቋም መረጃዎችን መመዝገብ፣ ማጠናቀር፣ መተንተንና በአለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት መለዋወጥ እንዲሁም መረጃዎቹ የሀገር ሀብት እንደመሆናቸው ለተተኪ ትውልድ ጠቀሜታ እንዲውሉ ማከማቸት፣
- ኤጀንሲው ያቋቋማቸው የሚቲዎሮሎጂ ቅ/ጽ/ቤቶችን በሰው ኃይል፣ በዘመናዊ የመገናኛ አዉታር በሌሎች ፋሲለቲዎች በማጠናከር መንግሥት ለጀመረው የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ለማሳካት በተቋቋሙባቸው ክልሎች አስፈላጊውን የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት በብቃት እንዲሰጡ ማድረግ፣
- ከአየር ጠባይ ገጽታዎች ለታዳሽ የኃይል ምንጮች (Renewable energy) አጠቃቀም ግብአት የሚሆን የንፋስና የፀሐይ ጨረር ኃይል እምቅ ሀብቶች ጥናት ለማካሄድ የሚያስችሉ የትንተና አገልግሎቶች ማጠናከር ይሆናል፡፡

## 1.2.1 የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች አውታር

የአንድ አገር የኢኮኖሚ ልማትና እድገት በአየር ሁኔታ ጠባይ መረጃ በመደገፍ የአየር ጠባይ ሀብቶችን በሚገባ ለመጠቀም የመረጃ ምንጭ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች አውታር ማቋቋምና ማጠናከር የመጀመሪያው አቢይ ተግባር ሊሆን ይገባል፡፡

የአገሪቱን ልዩ ልዩ ክፍሎች የአየር ሁኔታና ጠባይ ክትትልና የትንበያን ሽፋን እንዲሁም የጥራት ደረጃዎች (Resolution and quality standard) የጠበቀ አገልግሎት ለመስጠት አገሪቱ ካላት የቆዳ ስፋትና የመልካ ምድራዊ ሁኔታ ሊሟላ የሚገባው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መረብ በቅርቡ ጥናት የተካሄደበት የጣቢያዎች ኔትወርክ ማስተር ፕላን በሰንጠረዥ እንደሚከተለው ያመለክታል ፡፡

ሠንጠረዥ-1: በጣቢያዎች ኔትዎርክ ማስተር ፕላን መሠረት የጣቢያዎች ብዛት የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ተራ ቁጥር | በኤጀንሲው የሚገኙ የጣቢያዎች ዓይነት | ወደፊት የሚቋቋሙ ጣቢያዎች (ብዛት) | አሁን ያሉት የጣቢያዎች ብዛት | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሳይኖፕቲክ * | 12 | 18 | 30 |
| 2 | ጠቋሚ | 15 | 162 | 177 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3 | 3ኛ | 55 | 507 | 562 |
| 4 | የዝናብ ዘጋቢ (4ኛ) | 41 | 410 | 451 |
| 5 | የተሟላ መረጃ ያላቸው የተዘጉ ጣቢያዎች** | | 600 | 600 |
| | ድምር | 123 | 1697 | 1820 |

* ሲኖፕቲክ ጣቢያዎች የኤሮኖቲክስ ጣቢያዎችን ያጠቃልላል፡፡

** በተለያየ ምክንያት አገልግሎታቸዉን ያቋረጡ ነገር ግን መረጃቸዉ በአረካይቭ (Archive) ተቀምጦ በተጠቃሚ ሲፈለግ ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉትን ጣቢያዎች ያጠቃልላል፡፡

ከለይ በሠንጠረዥ-1 የተጠቀሱት የምድር መረጃ መሰበሰቢያ ጣቢያዎች የተለያዩ ደረጃዎች ያሏቸዉ ሲሆን አሁን ያሉት ጣቢያዎችንም ሆነ ወደፊት የሚቋቋሙት ጨምሮ የጣቢያዎቹ ስርጭትና ትክክለኛ ቦታ ከየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ጋር በሚደረግ ምክክርና ክትትል የሚወሰን ይሆናል፡፡

በሌላም በኩል በዚህ ማስተር ፕላን ጥናት መሠረት በአምስት ዓመቱ የኤጀንሲዉ የስትራቴጂክ ዕቅድ ማጠቃለያ ላይ በሀገሪቱ የሚኖሩት የሳይኖፕቲክና ኤሮኖቲክስ ጣቢያዎች አሁን ሊቋቋሙ የታቀዱት 12 ጣቢያዎቸ ጨመሮ በአጠቃላይ ቁጥራቸዉ 30 የሆነ የሳይኖፕቲክና ኤሮኖቲክስ ጣቢያዎቸ ይኖራሉ፡፡

*ሠንጠረዥ- 2: በጣቢያዎች ኔትዎርክ ማስተር ፕላን መሠረት በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ ያሉና ወደፊትም ለተለያየ ጥቅም የሚያገለግሉ ሆነዉ ሊቋቋሙ የተጠኑ (Special) የመረጃ መሰበሰቢያ ጣቢያዎች የሚያሳይ ዝርዝር፡፡*

| ተራ ቁጥር | በኤጀንሲው የሚገኙ የጣቢያዎች ዓይነት | ወደፊት የሚቋቋሙ ጣቢያዎች (ብዛት) | አሁን ያሉ ጣቢያዎች ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ ጣቢያ* | 6 | 9 |
| 2 | የከፍታ አየር መዝጋቢ | 5 | 3 |
| 3 | የአየር ብክላ መመዝገቢያ ጣቢያ | 2 | 0 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4 | ዲጂታል የነፋስ ጣቢያ (DWS) | 7 | 4 |
| 5 | ከሳተላይት የሚቲዎሮሎጂ መረጃ መቀበያ ጣቢያ | 13 | 2 |
| 6 | Awutomatic Weather station (AWS) | 187 | 20 |
| 7 | ራዳር | 2 | 0 |
| 8 | Automatic weather observation System (AWOS) | 5 | 5 |
| | ድምር | 227 | 43 |

በመላ ሀገሪቱ ያስፈልጋሉ ተብሎ ከተጠናው የጣቢያዎች ስታንዳርድ አንፃር ሲታይ አሁን በሥራ ላይ ያሉት 1097 ጣቢያዎች ቀደም ሲል ይሰሩ ከነበሩና የተወሰነ መረጃ ያለቸው ወደ 600 የሚጠጉ የተለያየ ደረጃ የነበራቸው የተዘጉ ጣቢያዎች ጋር 1697 የሚጠጉ ጣቢያዎች መረጃ እንደሚገኝ ይታመናል። በማስተር ኘላኑ መሰረት ለሀገሪቱ ያስፈልጋል ተብሎ የሚገመተውን (surface observing stations) ወደ 1820 የሚጠጋ የጣቢያዎች ቁጥር ለመድረስ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በተያዘው በጀት ዓመት 123 ጣቢያዎችን በማቋቋም የማስተር ኘላኑን የ5 ዓመት ግብ መምታት ይቻላል።

### 1.2.2 <u>ጥራት ያለዉ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰብሰብ</u>

በአገራችን የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መስጠት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ኤጀንሲዉ መረጃዎችን በመሰብሰብ በማጠናቀርና በመተንተን ለልዩ ልዩ ጥናቶች ምርምር አገልግሎት፣ የተፈጥሮ አደጋን ለመከላከል፣ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አገልግሎት ለመስጠትና ለሌሎች ልዩ ልዩ የልማት ዘርፎች እንቅስቃሴ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን በመጠቀም የአጭር የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ የትንበያ እና የምክር አገልግሎት ሲያበረክት ቆይቷል፡

የሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎችን በቅርብ ሆኖ በማቋቋም አስተማማኝ እና ጥራት ያለዉን መረጃ ለመሰብሰብ ያልተማከለ አስተዳደርንም በመዘርጋት የእርሻ ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መጠቀም እንዲችል፣ ኤጀንሲዉ 11 ቅ/ጽ/ቤቶችን በማቋቋም ለክልሉ የግብርናና ሌሎች ዘርፎች የቅርብ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

ኤጀንሲዉ ከክልሎች ጋር በኢንተርኔት፣ በፋክስ፣ በቴሌፎንና በመገናኛ ሬዲዮ የመረጃዎች ልዉዉጥ ያደርጋል፡፡ ከ2000 - 2004 ባለዉ የስትራቴጂክ ዕቅድ ንድፍ በኢንተርኔትና በዌብሳይት ያለዉ ግንኙነት መሰረት የተጣለ ሲሆን፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ከማዕከል አስተዳደር ጋር የተጠናከረ ግንኙነት እንዲኖራቸዉና የመረጃዉም ፍሰት ጥራቱ እየጨመረ እንዲሄድ የመገናኛ መስመሮች ከአሁኑ በተሻለ መንገድ የተጠናከረ ሊሆን ይገባል፡፡

ለብሄራዊና ለአለም አቀፍ የአየር ጉዞ የሚረዳ የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ የአየር ትራንስፖርት በአስተማማኝ ሁኔታ ደህንነቱ የተጠበቀ ቀልጣፋ እና ኢኮኖሚያዊ ለማድረግ የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ለማሳደግ ኤጀንሲዉ ካደረገዉ ጥረት አኳያ በዘጠኝ አየር ማረፊያዎች ላይ የሚሰጠን ትንበያ ወደ 15 እንዲያድጉ ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት በአራት የአየር ማረፊያዎች የአዉቶማቲክ የአየር ሁኔታ ኦብዘርቬሽን ሲስተም መሳሪያ ተተክሎላቸዋል፡፡ ለአየር ማረፊያዎች የተሻለ የኤሮኖቲካል መረጃ እንዲያበረክቱ ሲሆን በሀገር አቀፍ ደረጃም በአምስት ብሄራዊ ኤርፖርቶች የንፋስ አቅጣጫ መሳሪያ በመትከል የመረጃዎቹ ጥራትና ፍሰት የተሻለ እንዲሆን ጥረት እየተደረገ ነዉ፡፡ ለወደፊቱም የኤሮኖቲል ሚቲዎሮሎጂ መረጃን ጥራት ለመጠበቅ በዘመናዊ የመገናኛ መሳሪያዎች መደራጀት ወሳኝና አሌ የማይባል ጉዳይ ነዉ፡፡

# 2 የኤጀንሲዉ አመሰራረት፣ ሥልጣንና ተግባር ትንተና

## 2.1 የኤጀንሲዉ አመሰራረት

በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ወደ አገሪቱ በገቡ አሳሾችና ሚሲዮናውያን ድርጅቶች አማካይነት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በተቋቋሙ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች በሚሰበሰብ መረጃ እንደተጀመረና

በጠላት ወረራ ጊዜም ከተለያዩ አካባቢዎች የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ይሰበሰብ እንደነበር እሙን ነው፡፡ ከ1938 እስከ 1943 ዓ.ም ከአንበጣ መከላከያና ከእርሻ ማስፋፊያ ፅ/ቤቶች ሥራዎች ጋር በተገናኘ የተወሰነ የሥራ ጅምሮች እንደነበሩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨመማሪም የአዋሽ ተፋሰስና ሃይድሮሎጂ መምሪያ ከ130 በላይ የራሳቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያ በማቋቋም መረጃ ይሰበስቡ ነበር፡፡ ከዚያም በኢትዮጵያ ከበረራ ሥራ አጀማመር ጋር በተገናኘ መልኩ ከ1943 ዓ.ም ጀምሮ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የአቪየሽን መገናኛ አገልግሎትን ለማገዝ ሲባል በሲቪል አቭዬሽን መሥሪያ ቤት ውስጥ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች መሰብሰብና ለበረራ አገልግሎት ማዋል በስፋት ተጀመረ፡፡ በመቀጠልም የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ያለው ጠቀሜታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱና የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላዊ በሆነ መንገድ መስጠት በማስፈለጉ መንግስት ታህሳስ 22 ቀን 1973 በአዋጅ ቁጥር 201/73 የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ድርጅትን የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት እንዲሰጥ አገሪቱ ሚቲዎሮሎጂን በሚመለከት በአለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት ያለባትን ግዴታ በተሻለ ሁኔታ መወጣት እንድትችል የሚያደርግ ዓላማዎች ያሉት ድርጅት ሆኖ ተቋቋመ፡፡

## 2.2 **የኤጀንሲዉ ሥልጣንና ተግባር ትንተና**

ኤጀንሲው ሲቋቋም ከዚህ የሚከተሉት ዋና ዋና ሥልጣንና ተግባራት ተሰጥተውታል እነርሱም፣

1. የልዩ ልዩ ብሔራዊ የሥራ እንቅስቃሴዎችና የልማት ፕሮግራሞችን ፍላጎት የሚያሟሉና ኢትዮጵያን የተፈጥሮ አካባቢዎች የሚውክሉ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎችን በአገሪቱ ውስጥ ማቋቋምና ማካሄድ፣
2. የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን በሙሉ መሰብሰብ፣
3. ኢትዮጵያ ተዋዋይ በሆነችባቸው የኢንተርናሽናል ስምምነቶች መሰረት የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን መለዋወጥ፣

4 የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለማሰራጨት የሚያስችሉ የመገናኛ ዘዴዎችን በህግ መሰረት ማቋቋምና ማካሄድ፣

5 የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችንና የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ ውጤቶችን ማሳተምና ማሰራጨት፣

6 ስለ አስጊ የአየር ሁኔታ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣ ምክርና ትምህርት አዘል መግለጫዎችን በየጊዜው በህዝብ መገናኛ ዘዴዎች ማሰራጨትና በሚጠየቅበት ጊዜ ለማንኛውም አካል የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መስጠት፣

7 በአገሪቱ ውስጥ የተሰበሰበውን ማናቸውንም የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ማዕከላዊ በሆነ መንገድ ማከማቸትና ማስተዳደር፣

8 በልዩ ልዩ ኬሚካሎች አማካኝነት የአየር ብክለት እንዳይከሰት ክትትል ማድረግና ዉጤቱን አጥንቶ ማቅረብ፣

9 ማንኛውም ሰው የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ለመመዝገብና ለመሰብሰብ ሲጠይቅ አስፈላጊነቱን አመዛዝኖ መፍቀድ፣

10 ሚቲዎሮሎጂን በሚመለከት ረገድ በኢንተርናሽናል ደረጃ ተወስነው መንግስት ያፀደቃቸውን ስምምነቶች በሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፣

11 ስለሚቲዎሮሎጂ ጥናትና ምርምር ማካሄድ ጠቃሚ ውጤቶችንም በሥራ ላይ ማዋል፣

12 ለሚሰጠው አገልግሎት የአገልግሎት ዋጋና ልዩ ልዩ ክፍያዎችን አግባብ ባለው የመንግስት መሥሪያ ቤት አስወስኖ ዋጋ ማስከፈል፣

13 ሚቲዎሮሎጂን የሚመለከት ማናቸውንም ስብሰባ ጉባኤ ወይም ሴሚናር መንግስትን ወክሎ መሳተፍ ናቸው፡፡

ሆኖም አየር ብክላ ጣቢያዎችን በማቋቋም የመረጃ ምዝገባና ክትትል ማድረግ ትኩረት ተሰጥቶት ሊከናወን የሚገባ ይሆናል፡፡ ከዚህም ሌላ በአንድ ወቅት ኤጀንሲዉ በአገሪቱ በተለያዩ ቦታዎች የርዕደ- መሬትን ክስተት ለመከታተል የሚያስችሉ ጣቢያዎች የማቋቋምና የርዕደ-ምድርን /Earth Quake/ መረጃዎች እንዲሰበስብ ሀሳብ ቀርቦ የነበረ ቢሆንም ሥራው በቀጥታ ከከባቢ አየር ይልቅ በመሬት ውስጥ እንቅስቃሴና ከሥነምድር ጋር የተዛመደ በመሆኑ ተግባራዊ አልሆነም፡፡ አሁንም ቢሆን መንግስት ጉዳዩን የሚከታተል ባለበት ሰይሞ ስራው እንዲሰራ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

በአጠቃላይ ኤጀንሲዉ በአሁኑ ወቅት የአገር ውስጥና ከአለም አቀፍ ምንጮች የሚሰበሰበውን የሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰረት በማድረግ ለአገሪቱ ልዩ ልዩ ማህበራዊና

ኢኮኖሚያዊ ልማት በግብዓትነት እንዲያገለግሉ መረጃዎችን ያጠናቅራል፣ ይተነትናል እንዲሁም ያከማቻል፣ በአየር ሁኔታ መዛባት ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችን ለመከላከል የሚያስችል የአየር ሁኔታ ትንበያና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አገልግሎት ይሰጣል፣ ለአለም አቀፍ በረራ አገልግሎት የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን ይሰጣል፣ በዘርፉ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያከናውናል፣ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣ አገሪቱ አለም አቀፍ ስምምነቶች እንድትወጣ አስፈላጊውን ሥራ ያከናውናል፡፡

## 2.3 ኤጀንሲዉ ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራትና ያጋጠሙት ችግሮች

### 2.3.1 የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

የህብረተሰቡን የአየር ሁኔታ መረጃን ፍላጎት ለማርካት ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ድርጅት ጋር በመተባበር የአየር ሁኔታ መግለጫዎችን በየዕለቱ ህብረተሰቡ የየእለቱን የአየር ሁኔታ ክስተት እንዲከታተል አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ ይህም የጎጂ አየር ሁኔታ ክስተት ጉዳትን ለመቀነስ ህብረተሰቡ የበለጠ ዝግጁ እንዲሆን አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

ኤጀንሲዉ ለግብርናው መስክ ጠቀሜታ ያለው የአግሮክላይማቲክ ቀጠናዎች ጥናት ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር በማካሄድ ለልማት ሥራዎች እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ፈላጊዎችን ለማርካትና የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን ለገበሬው ህብረተሰብና ለሌሎች የመረጃ ተጠቃሚ የህብረተሰብ ክፍሎች ለማዳረስ ኤጀንሲዉ የአገሪቱን መልካዓ-ምድራዊ ክፍፍልን በሚወክል መልኩ የሚቲዎሮሎጂ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶችን በማቋቋም አገልግሎቱን በስፋት፣ በጥራትና በጊዜ ለማዳረስ ጥረት ተደርጓል እየተደረገም ነው፡፡

ኤጀንሲው ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ለልዩ ልዩ ዘርፎች ለእርሻ፣ ለትራንስፖርት፣ ለኢንቨስትመንት፣ ለጤና፣ ለግንባታ፣ ለህይወትና ንብረት መጠበቅ ሥራዎች አስፈላጊውን የሚቲዎሮሎጂ መረጃ በመስጠት ሂደት ውስጥ ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል፡፡ በአለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት፣ በአየር ጠባይ ለውጥ (Climate Change)፣ በኦዞን ንጣፍ መሳሳት (Ozone depletion) በTechnological Need

Assessment በኩል በአገርና በአህጉር ደረጃዎች የተለያዩ ጥናታዊ ሥራዎች፣ ስበሰባዎችና ወርክሾፖች ተካሂደዋል፡፡

የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ባልተጠናከሩባቸው ከአብዛኛዎቹ የአፍሪካ ሀገሮች ከ1980ዎቹ ጀምሮ የወቅት የአየር ጠባይ ትንበያን ተግባራዊ በማድረግ የትንበያው አስተማማኝነት በተሻለ ደረጃ ላይ የሚመደብ ከመሆኑም በላይ የህብረተሰብ ክፍል በአህጉራዊና ዓለምአቀፋዊ ማዕከላትም እምነት የተጣለበት መሆኑ ተጨባጭ መረጃዎች አሉ፡፡ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያዎችን ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች አገልግሎት እንዲውል በማድረግ በሁሉም የበኩሉን አስተዋፅኦ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በተጨማሪም ኤጀንሲዉ ከሃያ ዓመታት በላይ መግለጫዎችን በማሰራጨትና ከህብረተሰቡ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ሳይንሳዊ ትንታኔ የመስጠቱን አካሄድ በተጠናከረ ሁኔታ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡

የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎችን ለማቋቋም፣ ለማጠናከርና ደረጃቸዉን በተገቢዉ ሁኔታ ለማሻሻል፣ የአገሪቱ መልክአ ምድራዊ ገጽታ አቀማመጥ በሚወክል የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ኔትወርክ ስርጭትን በመጠንና በዓይነት ለመወሰን የሚያስችል ጥናት ተካሂዷል፡፡ የአደረጃጀት ችግርና የስራ ድግግሞሽ ችግር እንዲቀረፍ የሰዉ ሀይል የፋይናንስ የንብረት አስተዳደርና የትራንስፖርት አገልግሎት በቅልጥፍናና ጥራት ለመስጠት የሚያስችል ስርዐት ተዘርግቶአል፡፡ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በማቋቋም ያልተማከለ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት አሰጣጥን በሚፈለገዉ ለመተግበር እንዲቻል፣ ጽ/ቤቶቹ በሚያስፈልጋቸዉ ቁሳቁስና የቢሮ ዕቃዎች በማደራጀት መረጃዎችን ከዋናው መ/ቤትና ከሌሎች የመረጃ ምንጮች እንደሚያገኙ እንዲሁም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የሚያወጡአቸዉን መጽሄቶች በድረገጽ በማሰራጨት እድገት በማሳየት ላይ ይገኛሉ፡፡ በግብርናዉ ክፍለ ኢኮኖሚ የተሰማሩ ባለሙያዎችን ከድርቅ ጋር በተገናኘ በሚከሰት አደጋ ኢንሹራንስ የሚገቡበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ከአለም የምግብ ድርጅት ጋር /FAO/ ህብረት በመፍጠር የተከናወነ ተሞክሮ አበረታች ዉጤት አስገኝቷል፡፡

## 2.3.2 ያጋጠሙ ችግሮች

1. የሚቲዎሮሎጂ መረጃ በቦታ፣ በጊዜና በዓይነት በበቂ ሽፋን ተሟልቶ አለመገኘት፣
2. የሚሰበሰቡ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች በቀላሉ ለተጠቃሚ ተደራሽ (accessibility) አለመሆን፣
3. የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ጥራት መጓደል፣
4. እሴት የታከለባቸው የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አናሳ መሆን፣
5. ቀልጣፋ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ለመስጠት የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አቅምና ስርአት አለመኖር፣
6. የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን በቅ/ጽ/ቤቶች እና በጣቢያዎችን አጠናክሮ ለመስጠት የሚያስችል አቅምን አለመኖር፣
7. የአጭር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ትንበያዎች ተጠቃሚዎች በሚፈልጉት ጥራት ጊዜና ቦታ አንጻር ማቅረብ አለመቻል፣
8. ለአውሮፕላን በረራ ደህንነት ከተገልጋዮች የሚጠበቀውን አገልግሎት ለማቅረብ አቀም ማነስ፣
9. በግብርና በውሀ በኢነርጂና በጤና መስክ በተጠቃሚዎች የሚፈለጉ አገልግሎቶችን ለማቅረብ አቀም ማነስ፣
10. በልዩ ልዩ የአገልግሎት ዘርፎች የሰለጠነ የሰዉ ሀይል በብቃት ተሟልቶ አለመገኘትና የሚቲዎሮሎጂ ቴክኒሽያኖች የሚሰለጥንበት ማዕከል አለመኖር፣
11. በሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎችና አጋዥ ቁሳቁሶች ጥገና ለማድረግ አቅም ማነስ፣ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ዘጋቢ የሆኑ መሳሪያዎች በብዛት ያለመስራት፣ እንዲሁም የሚመረቱ የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች ጥራትና ጥንካሬ ማነስ ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

በአጠቃላይ ከሀገር ውስጥና ከአለም አቀፍ ምንጮች የሚሰበሰቡ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች መሰረት በማድረግ ለአገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ስራዎች በግብዓትነት የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶች ሲያበረክት ቆይቷል፡፡ ለወደፊቱም መንግስት ለነደፈው ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ስኬታማነት የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት በተጠናከረ ሁኔታ ለመስጠት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

## 3. የኤጀንሲው ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች

## 3.1 የኤጀንሲው ራዕይ

ለኢትዮጵያ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት የሚያግዝ ዓለም አቀፋዊ ደረጃዉን የጠበቀ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም እዉን ማድረግ፣

## 3.2 የኤጀንሲው ተልዕኮ

የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀት፣ በመተንተን፣ በማጥናትና በመተንበይ ለሀገሪቱ የልማት እንቅስቃሴዎች ለእርሻ፣ ትራንስፖርት፣ ለኢንቨስትመንት፣ ለግንባታ፣ ለህይወትና ንብረት መጠበቅ እንዲሁም ለአየር ጠባይ መለወጥ ጥናትና ክትትል እገዛ የሚያደርግ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መስጠት፣

## 3.3 የኤጀንሲው ዕሴቶች

- ጥራት ያለው፣ ወቅታዊና አስተማማኝ የሆነ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ለደንበኞች መስጠት የአገልግሎታችን መለያ ነው፡፡
- በቡድን መስራትና ለሙያችን ታማኝ መሆን መመሪያችን ነው፡፡
- የአየር ሁኔታና ጠባይ ተፅዕኖዎችን አስቀድሞ መተንበይ የብቃታችን መለኪያ ነው፡፡

# 4 የባለድርሻዎችና የተባባሪዎች ትንተና

## 4.1 የባለድርሻዎች ትንተና

| ተ.ቁ. | የኤጀንሲዉ ባለድርሻዎች | ከኤጀንሲዉ የሚጠብቁት | የባለድርሻው ፍላጎት ባይሟላ ሊደርስ የሚችለው ተፅዕኖ | የተፈላጊነት ደረጃ | ኤጀንሲዉ መውሰድ የሚገባው እርምጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 4.1 የኤጀንሲው የዉስጥ ባለድርሻዎች | | | | | |
| 1 | የበላይ የሥራ አመራር | • የኤጀንሲዉ የሥራ ዘርፎች ተልዕኮአቃውን በተገቢው ሁኔታ መወጣት | • በዘላቂ ልማት ላይ ጎጂ ተጽዕኖ ማሳደር<br>• በአየር ሁኔታና ጠባይ መዛባት ለሚከሰቱ አደጋዎች ቅድመ ዝግጅት አለማድረግ<br>• መስኩ ለሀገሪቱ የልማት እንቅስቃሴዎች የሚያበረክተው አስተዋፅኦ አለመኖር<br>• ለጎጂ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መጋለጥ<br>• የኤጀንሲዉ ህልውና ጥያቄ ውስጥ መውደቅ | 1 | • ኤጀንሲዉ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችሉትን የጥናትና ምርምር ሥራዎች ማካሄድ<br>• ኤጀንሲዉ በሰው ኃይልና በመሣሪያ ተሟልቶ እንዲገኝ በማድረግ ኃላፊነትን እንዲወጣ ማስቻል<br>• አገራዊ አመለካከት ማምጣት<br>• ለስራዉ አመቺ የሆነ ድርጅታዊ መዋቅርና የአሰራር ስርዓት መዘርጋት |
| 2 | ሠራተኛው | • ምቹ የሥራ አካባቢ መኖር፣<br>• መልካም አስተዳደር (ግልፅነት፣ ሚዛናዊና ፍትሃዊ አስተዳደር)<br>• ሰራተኛዉ የሚያከናዉናቸዉን ስራዎች በተመለከተ የሚመዘንበት መለኪያ መኖር | • የሥራ ተነሳሽነት መቀነስ፣<br>• የሥራ ሥነምግባር አለመኖር፣<br>• ውጤታማነት መቀነስ፣<br>• የሠራተኛ ፍልሰት<br>• ኤጀንሲዉ ኃላፊነቱን መወጣት አለመቻል<br>• በዘፈቀደ ስራዎችን ማከናወን | 1 | • ሠራተኞች ተገቢውን ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣<br>• ግልጽና ተጠያቂነት ያለው የስራ ሁኔታዎችን መፍጠር የሰው ኃይል አስተዳደር ማስፈን፣<br>• የማትጊያ አማራጮችን ማመቻቸት<br>• ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎች እንዲሟሉ |

| ተ. ቁ. | የኤጀንሲዉ ባለድርሻዎች | ከኤጀንሲዉ የሚጠብቁት | የባለድርሻው ፍላጎት ባይሟላ ሊደርስ የሚችለው ተፅዕኖ | የተፈላጊነ ት ደረጃ | ኤጀንሲዉ መውሰድ የሚገባው እርምጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ማድረግ<br>• የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራሞችን ተግባራዊ ማድረግ ለእያንዳንዱ ሰራተኛ /የሙያ ዘርፍ የስራ ዝርዝር (Job description) በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ |
| 4.2 | የኤጀንሲው የውጭ ባለድርሻዎች | | | | |
| 1 | የውሃና ኢነርጂ ሚ/ር | የሚቲዎሮሎጂ አገልገሎትን በአግባቡ መካሄዱን<br>• የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የአየር ሁኔታ ትንበያ | • ለሀገሪቱ የልማት እንቅስቃሴዎች የሚቲዎሮሎጂ አስተዋፅኦ ማነስ<br>• ጎጂ የአየር ሁኔታና ክስተቶች ለመቀነስ የዝግጁነት መጓደል<br>• የኤጀንሲዉ ህልውና አደጋ ላይ መውደቅ<br>• በግድቦች ውስጥ ያለው ውሃ በቁጠባ ለመጠቀምና ደህንነት አለመቻል፤ | 1 | • የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ኔትወርክ ማስፋፋት<br>• የሠው ኃይል ብቃት ማሳደግ<br>• ዘመናዊ መሣሪያዎችን በመጠቀም የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መስጠት<br>• የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ለተጠቃሚዎች በቅርበት ማዳረስ<br>• የመንግስት ፖሊሲን ተግባራዊ ማድረግ<br>• የሚቲ.ጣቢያዎችን ማስፋፋት<br>• ዘመናዊ መሳሪያዎች (እንደራዳር) በመጠቀም የአየር ሁኔታ ክስተቶችን መከታተል፤<br>• በተፋሰስ ላይ የተመሰረተ የአየር ሁኔታ ትንበያና ክትትል |

| ተ.ቁ. | የኤጀንሲዉ ባለድርሻዎች | ከኤጀንሲዉ የሚጠብቁት | የባለድርሻው ፍላጎት ባይሟላ ሊደርስ የሚችለው ተፅዕኖ | የተፈላጊነት ደረጃ | ኤጀንሲዉ መውሰድ የሚገባው እርምጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 3 | ግብርና ሚ/ር | • እያንዳንዱ የዝናብ ወቅት ከመግባቱ በፊት የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያን (የዝናብ አጀማመር፣ መጠን ስርጭትና አወጣጥ)<br>• ወቅታዊ ባልሆኑ የአየር ሁኔታዎች ላይ ክትትል ለማድረግ የሚያስችሉ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያዎች<br>• ለተባዮች መከሰት አመቺ የአየር ሁኔታዎች በሚኖርበት ጊዜ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያን<br>• ለአርብቶ አደሩ አካባቢ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያዎች መስጠት፣<br>• በሰብል መሰብሰብ ወቅታዊ ያልሆነ የዝናብ ክስተት ትንበያ<br>• በደረቅ ወቅት እሳት አደጋን ሊያስከትሉ በሚችሉ የነፋስና የከፍተኛ ሙቀት ክስተቶች ላይ የቅድሚያማስጠንቀቂያ | • የግብርና ሥራ እንቅስቃሴዎች በተለምዶ እንዲከናወን ማድረግ<br>• ለግብርና ግብአት አቅርቦት በቂ ዝግጅት አለማድረግ<br>• በሰበሎችና ዕፅዋት ላይ ጉዳት መድረስ<br>• በእሳት አደጋ ምክንያት በሰብልና በደን ላይ ውድመት መድረስ<br>• በአርብቶ አደሩ አካባቢየዉሀና የግጦሽ አቅርቦት አስቀድሞ ማቀድ አለመቻል፣ | 1 | • ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ በግብአትነት ሊያገለግል የሚችል የአየር ሁኔታ ትንበያን አስተማማኝ በሆነ መልኩ መስጠት መቻል<br>• የሀገሪቱ መልክአምድራዊ አቀማመጥን በሚወክል መልኩ ጣቢያዎችን ማቋቋም<br>• ጠቃሚና ጎጂ የአየር ሁኔታ ክስተቶችን በግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ ሚያሳድሩትን ተፅዕኖ በመለየት ሙያዊ ምክር መስጠት<br>• የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ለተጠቃሚዎች በቅርበት መስጠት<br>• የአርሶ አደሩና የአርብቶ አደሩ ህብረተሰብ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ጠቀሜታን ማሣወቅ |
| | | | | | |

| ተ. ቁ. | የኤጀንሲዉ ባለድርሻዎች | ከኤጀንሲዉ የሚጠብቁት | የባለድርሻው ፍላጎት ባይሟላ ሊደርስ የሚችለው ተፅዕኖ | የተፈላጊነ ት ደረጃ | ኤጀንሲዉ መውሰድ የሚገባው እርምጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 4 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል ኮርፖሬሽን | • የየዝናብ ወቅት የዝናብ ስርጭትና መጠን ትንበያ<br>• ለዲዛይንና ለኮንስትራክሽን አገልግሎት የሚውል የሚቲዎሮሎጂ መረጃ፤<br>• ለታዳሽ ሀይል ምንጭ ጥናትና ልማት የሚያገለግሉ መረጃዎች ማቅረብ (ፀሀይ፣ ንፋስ ወዘተ. . . ) | • በግድቦች የሚጠራቀመውን የውሃ መጠን በማወቅ የኃይል አቅርቦትን ለማቀድ አለመቻል<br>• ግድቦች ውሃን ከመያዝ አቅማቸው በላይ በሆነ ምክንያት በግድቦች ላይ የሚደርስ ጉዳትን አለመከላከል<br>• ከግድቦች ከፍተኛ መጠን ያለው ውሃ ሲለቀቅ በታችኛው ተፋሰስ ነዋሪዎችና በኢኮኖሚ ተቋማት ላይ ጉዳት ማስከተል<br>• በየግድቦች ያለውን ውሃ ከዕቅድ ውጭ በመጠቀም ለኃይል አቅርቦት ማነስ መዳረግ<br>• ለመስኖና ለመጠጥ ውሃ እጥረት መዳረግ | 1 | • በተፋሰሶች አካባቢ የሚጠበቀውን የዝናብ መጠንና ስርጭት በቅድሚያ በመተንበይ መረጃ መስጠት<br>• በተፋሰሶች አካባቢ ወካይ በሆኑ ቦታዎች ጣቢያዎችን ማቋቋም<br>• የረጅም ጊዜ የዝናብ ትንበያ ለመስጠትና ለጎርፍ መከሰት አስተዋፅኦ የሚኖራቃውን የአየር ሁኔታ ክስተቶች ተከታትሎ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መስጠት የሚያስችል አቅም ማሳደግ |
| 5 | የጤና ጥበቃ ሚ/ር | • የዝናብ ስርጭትና መጠን ትንበያዎች<br>• በደረቅ ወቅት የሚኖረው የአየር ሙቀት አዝማሚያ<br>• ወቅታዊ ባልሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ | • ከዝናብ ወቅት መርዘም፣ መጠናከር ወይም ማጠር እንዲሁም ከድርቅ ጋር ተያይዘው በሚከሰቱ በሽታዎች ላይ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ አለመቻል<br>• ለተላላፊና ወረርሽኝ በሽታዎች መጋለጥ | 2 | • በመስኩ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ትንበያ በአስተማማኝ መስጠት መቻል<br>• የሚቲዎሮሎጂ አገልገሎት ለጤናው ዘርፍ የሚያደርገውን አስተዋፅኦ በሚመለከት በጋራ ጥናትና ምርምር ማካሄድ |
| 6 | የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣንና የኤርፖርቶች ድርጅት | • ለበረራ ደህንነት የሚያስፈልገውን የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትማግኘት | • የአየር ትራንስፖርት ለአደጋ መጋለጥ<br>• አገልግሎቱን ፍለጋ ወደ ሌላ የመተላለፍ ዕድል መክፈት ዓለም አቀፍ ተጠያቂነት መከሰት | 1 | • የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን የአደረጃጀት ስርዓት አቅም በማሳደግ አስተማማኝ መረጃ መስጠት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተ. ቁ. | የኤጀንሲዉ ባለድርሻዎች | ከኤጀንሲዉ የሚጠብቁት | የባለድርሻው ፍላጎት ባይሟላ ሊደርስ የሚችለው ተፅዕኖ | የተፈላጊነ ት ደረጃ | ኤጀንሲዉ መውሰድ የሚገባው እርምጃ |
| 7 | ገበሬው | • የግብርና ምርትን ለማሳደግ የሚያስችል የእርሻ ሚቲዎሮሎጂ ምክር አገልግሎት ከአየር ሁኔታና ጠባይ መዛባት ጋር ተያይዞ ሊከሰቱ የሚችሉ ክስተቶችን በቅድሚያ ማወቅ ፣ | • የምርትና ምርታማነት አለማደግ፤<br>• የገበሬው የጎጂ የአየር ሁኔታዎች መቋቋም አለመቻል፤<br>• ገበሬዉ ከባህላዊ የአስተራረስ ዘዴ አለመላቀቅ፣ | 1 | • በቀጥታ ለገበሬው የሚደረስ የእርሻ ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መጀመር<br>• ከአየር ሁኔታና ጠባይ መዛባትና/መለዋወጥ ጋር ተያይዞ ሊከሰቱ የሚችሉትን አስቀድሞ በመተንበይ መረጃዎችና የምክር አገልግሎት መስጠት |
| 8 | ህብረተሰቡ | • ስለሚቲዎሮሎጂ ሣይንስ ግንዛቤ ማግኘት<br>• የዕለታዊ፣ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊና ወቅታዊ የአየር ሁኔታና ጠባይ ማወቅ<br>• ከአየር ሁኔታና ጠባይ መከሰት ጋር ተያያዥነት ያለዉ መረጃዎችን ማግኘት<br>• የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን በቀጥታ ማግኘት | • የህብረተሰቡ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በዘልማድ ላይ መመስረት<br>• በሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ተጽዕኖ ማሳደር<br>• ለሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ያለው የግንዛቤ ማነስ<br>• አስጊ የአየር ሁኔታ ዘገባዎች በቅድሚያ ለህብረተሰቡ አለመድረስ | 1 | • የህብረተሰቡን ፍላጎት የሚያሟላ የሚቲዎሮሎጂ መረጃን በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ማስተላለፍ መቻል<br>• የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ጠቀሜታ ህብረተሰቡ እንዲያውቅ የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት መስጠት<br>• ጥናትና ምርምር በማድረግ የትንበያን ጥራትና አሠጣጥ ዘዴን ማሻሻል<br>• የአየር ሁኔታና ጠባይ መረጃዎችንና መግለጫዎችን በተለያዩ ቋንቋዎች ማሰራጨት<br>• በየቅ/ጽ/ቤቶቹ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት አሰጣጥን ማሳደግ፣<br>• |
| ተ. | የኤጀንሲዉ | ከኤጀንሲዉ የሚጠብቁት | የባለድርሻው ፍላጎት ባይሟላ | የተፈላጊነ | ኤጀንሲዉ መውሰድ የሚገባው |

| ቁ. | ባለድርሻዎች | | ሊደርስ የሚችለው ተፅዕኖ | ት ደረጃ | እርምጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 8.1 | አርብቶ አደር | • ለከብቶች መኖ፣ ግጦሽና መጠጥ ውሀ አቅርቦት ክትትል የሚያግዝ የእፅዋትና የዝናብ መረጃ አገልግሎት | • የአርብቶ አደሩ የጎጂ አየር ሁኔታዎች ለመቋቋም አለመቻልና የሚደርሱትን ጉዳቶች ለመቀነስ አለመዘጋጀት፤ | 1 | • በቀጥታና በቅርቡ ለአርብቶ አደሩ የሚደርስ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማስጀመር |
| 8.2 | የግብርና ኢንቨስተር | • የተሻለና አዋጭ የሆኑ ሰብሎች ለማምረት የሚያስችሉ የአየር ጠባይ ሁኔታዎችን ከየአካባቢው ሊያገናዝቡ የሚችሉ የአግሮክላይማቲክ ምክር አገልግሎት | • ኢንቨስተሩ ሊከስር ይችላል<br>• ኢንቨስትመንት አይስፋፋም<br>• የስራ አጥነት ይኖራል<br>• ማህበራዊ ቀውሶች መፈጠር | 2 | • ኢንቨስተሮች ፈጣን የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የሚያገኙበትን ስርአት ማስፈንና አቅም ማሳደግ |
| 8.3 | ነጋዴውና ሸማቹ | • የሰብል ምርትና ገበያ ከአየር ጠባይና ሁኔታ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው አስፈላጊ የሆኑ ወቅታዊየአየር ትንበያ ምክርን ማቅረብ | • የገበያ አለመረጋጋት ሊፈጠር ይችላል<br>• ምርቶች ሊበላሹ ይችላሉ | 3 | የተጠናከረ የአየር ሁኔታና ጠባይ መግለጫዎች በየጊዜው በመገናኛ ብዙኃን መስጠትና ነጋዴውና ሸማቹ ተከታትሎ እንዲጠቀምበት የምክር አገልግሎት ማበርከት |
| 8.4 | ኮንስትራክሽን (የግንባታ ስራ ላይ የተሰማሩ | • የኮንስትራክሽን ስራን ለማቀድና ለመተግበር አስፈላጊ የሆኑ የአየር ጠባይ መረጃዎችና የአየር ሁኔታ ትንበያዎች ማቅረብ፤ | • የኮንስትራክሽን በወቅቱ አለመካሄድ<br>• ለተደጋጋሚ ወጪ የሚዳርጉ ዘላቂ ያልሆነ የኮንስትራክሽን ስራዎች እንዲካሄዱ መንገድ ይከፍታል፤ | 1 | • ፈጣን የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ስርአት ማስፈንና አቅም ማሳደግ |
| ተ. | የኤጀንሲዉ | ከኤጀንሲዉ የሚጠብቁት | የባለድርሻው ፍላጎት ባይሟላ | የተፈላጊነ | ኤጀንሲዉ መውሰድ የሚገባው |

| ቁ. | ባለድርሻዎች | | ሊደርስ የሚችለው ተፅዕኖ | ት ደረጃ | እርምጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 9 | የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር | • ዕቅድና የበጀት ፍላጎት በወቅቱ ተዘጋጅቶ እንዲደርሰው<br>• የአፈፃፀም መርሃግብርና የበጀት ድልድል<br>• ወርሃዊ የሂሣብ ሪፖርት<br>• ፕሮጀክት ፕሮፖዛል | • የበጀት አፈቃቀድና በድርጅቱ አገልግሎት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደር<br>• የበጀት በወቅቱ አለመለቀቅና የበጀት መመናመን<br>• ከዉጭ የሚገኝ እርዳታ መቀነስ | 2 | • በጊዜ ሠሌዳ መሠረት በመረጃ የተደገፈ የበጀት ፈላጎትና አፈፃፀም መርሃግብር እንዲሁም ሪፖርት አዘጋጅቶ ማቅረብ<br>• ስለሚቲዎሮሎጂ ሣይንስና ስለ ኤጀንሲዉ አገልግሎት ግንዛቤ ማስጨበጥ<br>• የመንግስትና የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ደንብን የተከተለ በጀት ማቀናጀትና ሪፖርት ማቅረብ |
| 10 | ፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር | • የሚቀርቡ የአደረጃጀትና የስራ ምደባ ጉዳዮች ጥያቄዎች በበቂ መረጃዎች እንዲደገፉ<br>• የሲቪል ሰርቪስ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ<br>በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ | • ከሥራ ጋር የተገናዘበ አደረጃጀት በጊዜዉ ተግባራዊ አለማድረግ፡<br>• ሥራን በአግባቡ አለመተግበር | 2 | • እያደገና እየሰፋ የሚሄደውን የኤጀንሲዉን አገልግሎት መሠረት ያደረገ በመረጃ ላይ የተመሠረተ የአደረጃጀት መረጃን ማዘጋጀት<br>ደንብና መመሪያን ተከተሎ መሥራት<br>የውስጥ መመሪያንና ደንቦችን በማዘጋጀትና በማፀደቅ ሥራላይ ማዋል |
| ተ. | የኤጀንሲዉ | ከኤጀንሲዉ የሚጠብቁት | የባለድርሻው ፍላጎት ባይሟላ | የተፈላጊነ | ኤጀንሲዉ መውሰድ የሚገባው |

| ቁ. | ባለድርሻዎች | | ሊደርስ የሚችለው ተፅዕኖ | ት ደረጃ | እርምጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 11 | ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር | • ለኤጀንሲዉ አገልግሎት የሚውሉ የህንፃ ግንባታዎች ደንብና መመሪያን መከተላቸውን ማረጋገጥ | • የህንፃ ግንባታ ፍቃድ ያለመስጠት | 3 | • በኮንስትራክሽን ህግ መሠረት ሥራዎች እንዲሠሩ ማድረግና መረጃዎች በወቅቱ እንዲቀርቡ ማድረግ .. |
| 12 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ | • የሬዲዮኖች ግዥ፣ ተከላና አጠቃቀም የኤጀንሲውን ደንብና መመሪያ መጠበቃቸውን፤ | • በየጣቢያዎች ለሚተከሉት ሬድዮኖች ፍቃድ ያለመስጠት<br>• የIT ዘመናዊ አገልግሎት አለመስጠት<br>• ኤጀንሲዉ የሚቲ.መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች በአግባቡ ማቅረብ አለመቻል፡ | 1 | • የኤጀንሲውን ደንብና መመሪያን ተከትሎ መሥራት<br>• ሬዲዮ የሚቋቋምበትን ትክክለኛ ስፍራ ከነመለያ ቁጥራቸው ማሳወቅ፣<br>• የሬዲዮ ፍሪኩየንሲ ማስደረግ፤<br>• የሬዲዮ ማስተላለፊያ ፈቃድ ማውጣት<br>• የITን አጠቃቀም ጥያቄ ማቅረብ<br>• የITን መሳሪያዎች ለተገቢዉ ግልጋሎት ማዋል |
| 13 | ትምህርት ሚኒስቴር | • የሀገሪቱን TVET ስርዓት የተከተለ የሚቲ. ሙያዎችን መለየት<br>• ስርዓተ ትምህርት እና የትምህርት መሳሪያዎች ማዘጋጀት | • የሀገሪቱን ደንብና መመሪያ ያልተከተለ የስልጠና አደረጃጀትና አሰጣጥ ከሌለ ፍቃድ ያለመስጠት<br>• በኤጀንሲዉ ተቋም የሰለጠኑ ባለሙያዎችን እዉቅና መከልከል | | • የሚቲ. ሙያዎችን መለየት<br>• ስርዓተ ትምህርትንና የማስተማሪያ መሳሪያዎችን መቅረጽ |

| ተ. | የኤጀንሲዉ | ከኤጀንሲዉ የሚጠብቁት | የባለድርሻው ፍላጎት ባይሟላ | የተፈላጊነ | ኤጀንሲዉ መውሰድ የሚገባው |
|---|---|---|---|---|---|

| ቁ. | ባለድርሻዎች | | ሊደርስ የሚችለው ተፅዕኖ | ት ደረጃ | እርምጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 14 | ክልላዊ ብሄራዊ መንግስታት | • የአየር ሁኔታና ጠባይ መረጃዎችና ትንበያዎች<br>• ከአየር ሁኔታና ጠባይ ጋር ተያይዞ በአጭር ፣ በመካከለኛና በረዥም ጊዜያት ሊከሰቱ የሚችሉ ጠቃሚ /ጎጂ ክስተቶችን በተመለከተ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መግለጫዎች | • መረጃዎች ለተጠቃሚዎች በተገቢዉ ቦታና ጊዜ አለመድረስ<br>• የሚቲዎሮሎጂ ቅ/ጽ/ቤት የተቋቋመበትን ተልዕኮ መፈጸም አለመቻል<br>• በኤጀንሲዉ ህልዉና ጥያቄ ዉስጥ መዉደቅ | | • የሚቲዎሮሎጂ ቅ/ጽ/ቤቶችን አቅም ማሳደግ<br>• የመረጃ ማሰባሰቢያ መለኪያ ዘዴዎችን ማጠናከር<br>• ተጠቃሚዎችን ያማከለ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን መስጠት |

| ተ.ቁ. | ተባባሪዎች | የትብብር መስክ | ከትብብሩ የሚገኝ ጠቀሜታ |
|---|---|---|---|
| 1 | የኢትዮጵያቴሌቪዥንና ሬዲዮ ድርጅት | • የአየር ሁኔታ ዘገባዎችና መግለጫ ለህብረተሰቡ ማስተላለፍ | • በህብረተሰቡ ዘንድ የሚቲዎሮሎጂ ሣይንስ አገልግሎት መታወቅ<br>• ኤጀንሲዉ የሚያስተላልፋቸው የቅድሚያ ማስጠንቀቂያዎች በወቅቱ ለህብረተሰቡ መድረስ |
| 2 | የኢትዮጵያ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር | • የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ለማጎልበት/ለማጠናከር የጥናትና ምርምር ሥራዎችን በጋራ ማካሄድ | • የሚቲዎሮሎጂን አገልግሎት ማሻሻል<br>• የጥናትና ምርምር ሥራ በጀት ድጋፍ |
| 3 | የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን | • የአየር ጠባይ ለውጥና ብክላ ዘርፍ በጋራ ክትትልና የጥናት ሥራዎችን ማካሄድ | • የውጭ ዕርዳታ ድጋፍ ማግኘት<br>• አለምአቀፋዊ ግዴታን በመስኩ መወጣት<br>• የአቅም ግንባታ |
| 4 | የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት | • የመረጃ ልውውጥ<br>• የጥናትና ምርምር ሥራ<br>• በአግሮሚቲዎሮሎጂ ዘርፍ ሚቲዎሮሎጂ ጠቀሜታን ስለማስፋፋት | • የአገልግሎት አሰጣጥን ማጠናከር<br>• የልምድ ልውውጥና የተሻለ ውጤት |
| 5 | የአርባምንጭ ዩኒቨርስቲ | • የሚቲዎሮሎጂ ባለሙያዎች ስልጠና<br>• ሙያዊ ልምድ ልዉዉጥ<br>• የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት<br>• የጋራ ጥናትና ምርምር ስራ ማካሄድ | • በኤጀንሲው የሚታየውን የሰው ኃይል እጥረት መቅረፍ |
| 6 | የዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት<br>WFP<br>ICPAC<br>FAO ወዘተ | • የመረጃ ልዉዉጥ<br>• የቴክኒክ እና የስልጠና ትብብር | • የቴክኒክ ድጋፍ<br>• የሰዉ ሀይል ልማት<br>• ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጋር መተዋወቅ<br>• የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል<br>• የሳተላይት መረጃዎችና ልዩ ልዩ የትንበያ ዉጤቶችን በነጻ ማግኘት |

| ተ.ቁ. | ተባባሪዎች | የትብብር መስክ | ከትብብሩ የሚገኝ ጠቀሜታ |
|---|---|---|---|
| 7 | የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | • የጥናትና ምርምር ስራ<br>• መረጃ ልዉዉጥ | • የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስን ለተለያዩ ሶሽዮ ኢኮኖሚያዊ ሴክተሮች እንዲዉል ማስቻል<br>• የሚቲዎሮሎጂ መረጃን ለተለያዩ የምርምር ጥናት ስራና ሶሺዮ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዲዉል ማስቻል |
| 8 | የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ | • የአየር ሁኔታና ጠባይ ካርታ ዝግጅት | • ደረጃውን የጠበቀ የሚቲዎሮሎጂ ካርታ ማግኘት<br>• የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል፣ |
| 9 | የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር | • የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ሂደቱን መከታተል | • ፆታዊ እኩልነትና የወጣቶች መብት ማስጠበቅ |

## 5. የኤጀንሲው ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች

በኤጀንሲው ዉስጣዊና ዉጫዊ ሁኔታዎች ቅኝትና የባለድርሻዎች ትንተና በተገኘዉ ዉጤት መሰረት የኤጀንሲው አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል ትኩረት የሚሹ ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች ተለይተዉ እንደሚከተለዉ ቀርበዋል።

1. መሰረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አቅርቦት አገልግሎትን በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ አለመቻል
2. የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን በዋናዉ መ/ቤት በቅ/ጽ/ቤቶች እና በጣቢያዎች አጠናክሮ ለመስጠት የሚያስችል አቅም ውስን መሆን፣
3. ወቅታዊና ጥራታቸውን የጠበቁ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችል አቅም ውስን መሆን
4. ሕብረተሰቡ ስለሚቲዎሮሎጂ ሣይንስና አገልግሎት ያለዉ ግንዛቤ አለመዳበር

# 6. የኤጀንሲዉ ዓላማዎችና ግቦች

## የኤጀንሲዉ ዓላማዎች

### ዓላማ 1

ከሀገሪቱ የኢንቨስትመንት መስፋፋት፣ የበረራ መጨመር እና የከተሞች እድገት ጋር የተጣጣመ የሚቲዊሮሎጂ ጣቢያዎች ሥርጭት እና ዓይነት (የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ኔትወርክ) ማሻሻል፣ የሚሰበሰቡትን መረጃዎች ተከታታይነት የተሟላ እና ጥራታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ማስቻል

### ግቦች (Objectives)

1. የአገሪቱን የአየር ሁኔታና ጠባይ ለመከታተልና ለመተንበይ እንዲቻል መልክአ ምድራዊና ስነ ምህድራዊ ወካይነት ሊያሟሉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ማቋቋም እና ተከላ ማካሄድ፣

| ተቁ | የጣቢያ ዓይነት | አሁን ያለበት | በ5 ዓመት የሚጠበቅ | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የገጸ ምድር የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያ | 1097 | 1223 | |
| 2 | አውቶማቲክ ጣቢያዎች(AWS) | 20 | 187 | |
| 3 | የከፍታ አየር ጣቢያ (AWS) | 2+1 | 5 | 1(AMU) |
| 4 | የራዳር ጣቢያ | 0 | 2 | 1 (MOWE) |
| 5 | የአየር ብክለት ጣቢያ | 0 | 2 | |
| 6 | የሚቲዎሮሎጂ ሳተላይት መረጃ መቀበያ ጣቢያ | 2 | 13 | በ11 ቅ/ጽ/ቤት (Low cost) |
| 7 | አውቶማቲክ ጣቢያ (AWOS) | 4 | 5 | |
| 8 | ዲጂታል የንፋስ ጣቢያ (DWS) | 4 | 7 | |
| 9 | ዲጂታል የንፋስ ጣቢያ (DWS) | - | 4 | upgrade |
| 10 | ከ4ኛ ወደ 3ኛ | - | 81 | ደረጃ ማሳደግ |

2. በቅ/ጽ/ቤቶችና በዋናዉ መ/ቤት የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች በዘመናዊ መንገድ ለማደራጀትና ለማስተዳደር የሚያስችል ወጥና ዘመናዊ የመረጃ ቋት ስርዓት (Climate data base management system) ማልማት፣

3. የተለያዩ የቢሮ ቁሳቁሶችና ተዛማጅ የቢሮ መገልገያ መሳሪዎችን ለ195 ጠቋሚ ጣቢያዎች ማሟላት

4. የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች የተሟላ የካሊብሬሽንና ጥገና ለማድረግ የሚያስችል የካሊብሬሽንና ጥገና ላብራቶሪ ዓቅም መገንባት (ለኮንቬንሽናልና ለአውቶማቲክ መሳሪያዎች)

5. የመረጃ ማጠናቀርና የክላይማቶሎጂ አገልግሎትን ማጠናከርና ታሪካዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች በኤሌክትሮኒክ ፎርማት እንዲቀመጡ የData rescue ሥራን ማካሄድ፣

6. መረጃን በቦታ ሽፋን ለማጠናቀር የሚያግዝ አንድ ደረጃዉን የጠበቀ የGIS (Spatial Analysis) ላቦራቶሪ ማቋቋም፣

7. የማሰልጠኛ ተቋም ማቋቋም

8. 50 የጠቋሚ ጣቢያዎች ቢሮዎችን ማቋቋም

## አላማ 2.

ኤጀንሲዉ የሚሰጠውን አገልግሎት በጥራትና በስፋት ለማሻሻል የሚያግዙ በተለያዩ የሚቲዎሮሎጂ አና ተዛማጅ ርዕሶች ላይ የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶችን ማዘጋጀትና ማካሄድ

## ግቦች

1. ወቅታዊ የሆኑ፣ ጥራታቸዉን የጠበቁና በአይነት የበዙ ለኤጀንሲዉ ኦፕሬሽናል ስራ የሚረዱ የምርምር ስራዎች፣ ጥናትና ምርምሮችን ማካሄድ፣
2. በኦዞን ስምምነቶች ዉስጥ የተካተቱ ግዴታዎችንና ሀላፊነቶችን ለመወጣት ኦዞንን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን በአማራጭ ኬሚካሎችና ቴክኖሎጂዎች መተካት፣

## አላማ 3.

የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ግቡን እንዲመታ ለማስቻል ድጋፍ አጠናክሮ መስጠት

## ግቦች

1. የሰው ሀይል አቅርቦት በበቂ ቁጥር ደረጃና ጥራት 100% ማሟላት
2. የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስና አገልግሎት ለሀገራችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለዉ በህብረተሰቡ ዘንድ የበለጠ ግንዛቤ ለመፍጠር በተለያዩ ዘዴዎች ሰፊ የማስተዋወቅ ስራ አሁን ካለበት 25% ወደ 50% ማሳደግ ፣
3. የህትመት ዉጤቱ የስርጭት መጠኑን ከ25% (ዝቅተኛ) ወደ 75% (ከፍተኛ) በማሳደግ ወቅታዊ መረጃ የያዘና የጥራት ደረጃዉ በማሻሻል ማሳደግ፣
4. የተቋሙን የስራ እንቅስቃሴ ለተገልጋዩ ወቅታዊና ቀጣይነት ባለዉ መልኩ ፕሬስ ኮንፈረንስ በማዘጋጀት በመስራት ከዚህ ቀደም በዓመት 4 ጊዜ ይሰጥ የነበረዉን በዓመት 9 ጊዜ መስጠት፣
5. የትራንስፖርት ስምሪትና ጥገና ዳታ ቤዙን በዘመናዊ መልክ መገንባት
6. በኤጀንሲዉ የሴቶች በሁሉም መስክ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚነት አሁን ካለበት 25% (ዝቅተኛ) ወደ 75% (ከፍተኛ) ማሳደግ ፣
7. የኤጀንሲዉን አላማ በተቀላጠፈ መልኩ ለማሳካት የሚያስችል የፊዚካል እና የበጀት ዕቅዱን ቅድሚያ ለሚሰጣቸዉ ዕቅዶች ከስትራቴጂክ ዕቅድ ጋር አጣጥሞ የጥራት ደረጃዉን አሁን ካለበት 75% ወደ 95% ማሳደግ፣
8. በኤጀንሲዉ ደረጃ የሚዘጋጁ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ጥራቱን ከ75% ወደ 96 % ማሳደግ፣

## ዓላማ 4

ከአየር ጠባይና ሁኔታ ጋር በተያያዘ መንገድ ሊከሰቱ የሚችሉ የተፈጥሮ አደጋዎችን አስቀድሞ በመተንበይና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በማካሄድ ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን መቀነስ እንዲሁም ለGTP ወይም ለግብርና፣ ለዉሀ ፣ ለኢነርጂና ለጤና ልማት፣ ለበረራ ወዘተ ለአገር ልማትና እድገት ሊዉሉ የሚችሉ ዘርፍ ተኮር አገልግሎቶችን ተግባራዊ ማድረግና ማጠናከር፣

## ግብ

1. የወቅት ትንበያ አሰጣጡ አሁን ከሚሰጠዉ ለአንድ ወቅት ቅድሚያ ትንበያን በማሳደግ ሁለት ወቅቶች አስቀድሞ መተንበይ፣ የቅድመ ጥቆማ አቅምን ማሳደግ፣
2. በየወሩ የሚሰጠዉን የአየር ጠባይ ትንበያን Climate Prediction Modelንና ስታቲስቲካል የትንበያ ዘዴዎችን በመጠቀም የቦታ ሽፋንንና የትንበያ መረጃን አስተማማኝነት በሚቀጥሉት አምስት አመታት በ100% ማሳደግ፣
3. በአሁኑ ጊዜ ተግባራዊ ያልሆነዉን የ Grass Root Agro-Meteorological Service (GRAMS) በሁሉም የሲኖፕቲክና ጠቋሚ ጣቢያዎች አማካይነት ለየአካባቢዉ የልማት ሰራተኞችና ገበሬዎች የግብርና ሚቲዎሮሎጂ የምክር አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ፣
4. ለአይሮፕላን በረራ አገልግሎት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ጥራታቸዉን እንዲጠብቁ ተደርጎ በጥንቃቄ ተቀምረዉና ተጠናክረዉ በአሁኑ ጊዜ በግማሽ ሰዓት የሚቀርበዉን ካለዉ የበረራ ተጠቃሚዎች ብዛት አንጻርን በ10 ደቂቃ ዉስጥ እንዲደርሱ ማድረግ፣
5. እስካሁን በጥሬ መረጃ ትንተና ላይ የተመሰረተውን የሀይድሮሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ደረጃውን በማሳደግ በተፋሰሶች ለሚካሄዱ ልዩ ልዩ የግንባታ ዲዛይን ሥራዎች ግብዓት ሊሆን የሚችል የዝናብ ትንተናን ተግባራዊ ማድረግ
6. ከአየር ሁኔታና ጠባይ ጋራ ተዛማጅ ለሆኑ የጤና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶችን ለምሳሌ ለወባ፣ ለማጅራት ገትር፣ ለአጣዳፊ የተቅማጥ በሽታና ለመሳሰሉት መንስኤ በሆነ የአየር ሁኔታና ጠባይ ክስተቶች ላይ ያተኮሩ የጤና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶችን ተግባራዊ ማድረግ

# 7. አካባቢያዊ ሁኔታዎች ቅኝት

## 7.1 ዉጫዊ ሁኔታዎች ትንተና

### 7.1.1 ፖለቲካዊ ሁኔታ

በህዝብ ተሳትፎና በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት ማህበራዊ ፍትህ የነገሰባት ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን ዕውን ማድረግ የህዝቡ ፍላጎት ነው። በአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት የተጀመረ ሲሆን፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን ጠንካራ መሰረት ላይ ለማቆም ከመንግሥት በኩል ከፍተኛ ቁርጠኝነት የሚታይበት ሁኔታ አለ። ምክንያቱም ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የህዝብ መብትና ጥቅም ለማስከበር የግድ መሟላት ያለበት ትልቅ ጉዳይ ነዉ። ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር በሰላማዊ ሁኔታ ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታን ይፈጥራል። ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር አገሪቱ ልትለማ የምትችልበትን የተስተካከለ ፖሊሲ ለመቅረፅ ያስችላል። የተስተካከሉ የልማት ፖሊሲዎች መቀረፃቸዉ ለልማት ተፈላጊ ሲሆን፣ የህዝቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በተከበሩበትና መልካም አስተዳደር በሰፈነበት ሁኔታ ፖሊሲዎችንና የልማት ኘሮግራሞችን ለመፈፀም ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።

አገሪቱ የፌደራል ሥርዓት አወቃቀርን ትከተላለች። በዚህም መሠረት ብሄር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እራሳቸዉን እንዲያስተዳድሩና የራሳቸዉ ጉዳዮች በእራሳቸዉ እንዲወስኑ ሥልጣን ተሰጥቷል። በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የአስተዳደር አካላት ነፃ ሆነዉ እንዲሰሩና የሶሽዮ-ኢኮኖሚዉ የልማት ማዕከል እንዲሆኑ ሁኔታዎች ተመቻችቷል። በመሆኑም እያንዳንዱ የአስተዳደር እርከን በአካባቢዉ ፈጣን ዕድገት በማምጣት የህብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ለመለወጥ እንዲቻል በየመስኩ እንቅስቃሴ በማካሄድ ላይ ይገኛል።

መንግሥት የግል ባለሀብቶች የአገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገት በማፋጠን በኩል የሚጫወቱት ሚና የላቀ እንዲሆኑ በመገንዘብ ባለሀብቶች በአገሪቱ ኢንቨስት እንዲያደርጉ የማበረታታትና አስፈላጊዉ የማጠናከሪያ ድጋፍ የማድረግ ፖሊሲ አለዉ። በዚህም መሰረት ሰፊ የኢንቨስትመንት አማራጮች ለባለሀብቶች ተከፍተዋል። ባለሀብቶቹ በኢንቨስትመንት

አማራጮቹ በመጠቀም ሰፋ ያለ የካፒታል ኢንቨስትመንት በተለያዩ የሥራ መስኮች በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

መንግሥት በተለያዩ መስኮች የአቅም ግንባታ ዕቅዶችን ነድፎ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። በልዩ ልዩ መስኮች እዉቀትና ክህሎት ያላቸዉ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በማፍራት የማቀድ፣ የማደራጀትና ኃይላቸዉን አስተባብረዉ ዕቅዶቻቸዉን የማስፈፀም አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ ሥልጠናዎች ተሰጥተዋል። በመሰጠትም ላይ ይገኛሉ። የአቅም ግንባታ ጥረቶች ዕቅዶቹን የማስፈፀም አቅም ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲሚያሻሽል ይገመታል።

የተለያየ የአየር ሁኔታና ጠባይ ክስተቶችን ሊቋቋሙ የሚችሉ ሰብሎች እንዲስፋፉ፣ እንዲሁም ገበሬው የሚቲዎሮሎጂ መረጃን በግበአትነት እንዲጠቀም፣ መንግስት በምርምር መሰከ አኳያ ከፍተኛ ድጋፍ በመስጠት ላይ ነው፡፡ አገሪቱ አሁን ካለችበት የእውቀት ደረጃ የተሻለ አድገት እነዲኖራት መንግስት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ከፍተኛ የአቅም ግንባታ ሥራዎች እንደ (Higher Level education and TVET Programm) በማስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ከፍ ሲል የተጠቀሱት ሁኔታዎች የሚቲዎሮሎጂ መረጃና አገልግሎት በግብዓትነት እንዲጠቀሙ የሚያደርጉና የኤጀንሲው የማስፈፀም አቅም የሚያድግበት በመሆኑ የአገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ ለሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት አመቺ ነዉ።

## 7.1.2 የኢኮኖሚ ሁኔታ

በአገሪቱ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት መንግስት ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ያደረገ ስትራቴጂ ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ግብርና ፈጣን ዕድገት ካመጣ የገጠሩን ህዝብ የኑሮ ደረጃ በቀጥታ በማሻሻል፣ ለኢንዱስትሪያዊ ዕድገት የሚሆን የጥሬ ዕቃና የካፒታል ምንጭ፣ እንዲሁም ለሀገር ዉስጥ የኢንዱስትሪ ምርቶች ገበያ በመሆንና ለከተማዉ ህዝብ ኑሮ መሻሻል ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረዉ ታምኖበት ተግባራዊ በመደረግ ላይ ነዉ። የልማት ስትራቴጂዉ አምራቾችን የሚያበረታታና ምርት እንዲጨምር የሚያግዝ ነዉ። እነዚህና በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ በመተግበር ላይ ያለዉ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ

(GTP) በአጠቃላይ ለሀገሪቱ ልማታዊ ዕድገት ልዩ ትኩረት የሚሰጡ ስለሆነ እንዲሁም የግል ኢንቨስትመንትና ቱሪዝም መስፋፋት ለሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትና መረጃ ተፈላጊነት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል። ኢኮኖሚዉን ለማሳደግ በመንግሥት በመወሰድ ላይ ያሉ እርምጃዎች ማለትም የመንገዶች መስፋፋት፣ የግል ኢኮኖሚን ማበረታታት፣ የቴሌኮሙኒኬሽንና የመብራት ኃይል ስርጭትና አቅርቦት ማስፋፋት የሚቲዎሮሎጂ ኔት ወርክን ለማስፋፋትና የሚቲዎሮሎጂ መረጃን በመሰብሰብ ለበረራ ደህንነትና ለሌሎች የልማት ሥራዎች የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትና መረጃ የሚረዳ በመሆኑ የኤጀንሲውን ሥራ በማቀላጠፍ በኩል ከፍተኛ እገዛ ይኖረዋል።

የአገሪቱ አጠቃላይ የአገር ዉስጥ ምርት ባለፉት አራት ዓመታት በተከታታይ ከ10% በላይ በየዓመቱ ማደጉን መረጃዎች (የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር) ያመለክታሉ። የሀገር ዉስጥ ምርት ማደግ መንግሥት ለልማት የሚመደበዉን በጀት አቅም የሚያጠናክር በመሆኑ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ለማሻሻል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

### 7.1.3 የማህበራዊ ሁኔታ

በአገሪቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የትምህርት ሽፋን እየጨመረ ቢሆንም ህብረተሰቡ በዘልማድ ከመንቀሳቀስ ዉጪ በሚቲዎሮሎጂ ሳይንስና አገልግሎት የመጠቀም ባህሉ አነስተኛ ነው ። በዚህም መሠረት ለሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ያለዉ አመለካከትም አናሳ ነዉ። እንደዚሁም የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስ ግንዛቤ አነስተኛ በሆነበት አካባቢ ያለዉን የአየር ሁኔታና ጠባይ ለመከታተል የተተከሉ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎችን ለመጠበቅ የመረዳት ችግር አለ። ይሁንና መንግሥት የተማረ ዜጋን ለመፍጠር እንዲቻል በየአካባቢዉ ትምህርትን በተለይም የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በማስፋፋት ረገድ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል። ከዚህ ጎን ለጎን ኤጀንሲው አሁን በመገናኛ ብዙኋን ከሚሰጠው መግለጫ በተጨማሪ የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስ እና ጥቅም አስመልክቶ ለህብረተሰቡ ለማሳወቅ ሰፊ ሥራ መስራት ይጠበቅበታል። ከፍተኛ የመንግሥት አካላት፣ የምርምር ተቋማትና መ/ቤቶች እንዲሁም የግሉ ሴክተር የሚቲዎሮሎጂ መረጃና አገልግሎት ለሚያካሂዱት

የልማት ሥራዎችና ጥናቶች አስፈላጊ ግብዓት መሆኑን ተገንዝበዉ በሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትና መረጃ መጠቀም እየጨመረ መጥቷል። እንዲሁም የአገሪቱ በድርቅ እና ጎርፍ በተደጋጋሚ መጠቃት የሚቲዎሮሎጂ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አገልግሎትን በህብረተሰቡ ዘንድ አስፈላጊነት እያጎላ መጥቷል።

የአገሪቱ የህዝብ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ በማደግ ላይ ነዉ። በሌላ በኩል የአገሪቱ ሀብት ዉስን ነዉ። ስለዚህ ሀብትን በአግባቡ በመጠቀም የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካትና ሀብትን ለመጪዉ ትዉልድ ለማስተላለፍ በአገሪቱ በሚካሄዱ የልማት ሥራዎች የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትና መረጃ በግብዓትነት መጠቀም ያስፈልጋል።

## 7.1.4 ቴክኖሎጂያዊ ሁኔታ

በቴክኖሎጂ አጠቃቀም አገሪቱ በዝቅተኛ ደረጃ ብትገኝም የኮምፒዉተሮች ጥቅም ላይ መዋል፣ የመገናኛ መሳሪያዎች መሻሻልና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሻሻል ኤጀንሲውን የሚነኩ ጉዳዮች ናቸዉ። የመገናኛ መሳሪያዎች ማለትም ቴሌፎን፣ ሬዲዮ፣ ፋክስ፣ ኢሜል፣ ኢንተርኔት፣ ሳተላይት፣ ወዘተ.. የኤጀንሲውን ግንኙነትና የመረጃ አሰባሰብና አሰረጫጨትን ፈጣንና ቀላል በማድረግ ላይ ይገኛሉ። የዘመኑ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ያልዳሰሰ ሰብዓዊ እንቅስቃሴ የለም። የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስና አገልግሎቱም የዚህ ቴክኖሎጂ ቀዳሚ ተቋዳሽ ናቸዉ። እንዲያዉም ያለ ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ማንኛዉም የሚቲዎሮሎጂ ተቋም አገልግሎት ለመስጠት የማይታሰብበት ዘመን ላይ እንገኛለን። ስለዚህ በተለምዷዊዉም ሆነ የዘመኑ የቅኝት መሳሪያዎች የሚሰበሰቡትን መረጃዎች ለማደራጀትና ለመተንተን በከፍተኛ ደረጃ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም አቅምን ማጎልበት ለአንድ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ወሳኝ ነዉ።

በሀገራችን ገጠራማ አካባቢዎች ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት እየተዘረጋ ያለው የመሰረተ ልማቶች በተለይም የኤለክትሪክ፤ የቴሌኮሙኒኬሽን እና የመንገድ ግንባታ ለኤጀንሲው አገልግሎት መቀላጠፍ ቀጥተኛ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል። በተጨማሪም በሀገራችን የተዘረጉት ዘመናዊ የሳተላይት መገናኛ አውታሮች (Schoolnet,

agrinet,weredanet,healthnet, etc) በአግባቡ ጥቅም ላይ ከዋሉ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ግብአት የሚሆኑ መረጃዎችን፤ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶች እና ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎችን ወደ ተጠቃሚዎች ለማዳረስ አመቺ ሁኔታዎችን ሊፈጥር ይችላል። በአንጻሩ በሀገራችን ያለው የኢንተርኔት አቅም ውሱንነት የኤጀንሲውን ዓለምአቀፋዊ እንዲሁም ከቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ጋር ያለውን የመረጃ ልውውጥ ላይ ከቴክኖሎጂው ሊገኝ የሚችለውን ጠቀሚታ ማግኘት አልተቻለም።

እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በድርቅ፣ ጎርፍና ተዛማጅ የሥነምህዳራዊ ችግሮች ተተብትቦ በተያዘ አገር ያለ የሚቲዎሮሎጂ ተቋም ከሁሉም በፊት ከሚጠበቁበት ዉጤቶች ጎላ ብለዉ የሚጠቀሱት ከተፈጥሮ አደጋ (እንደ ድርቅ እና ጎርፍ ካሉት) ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚያደርሰዉን ኢኮኖሚያዊ ኪሣራ የመቀነስና በልማት መርህ ግብርና ንድፍ ትልምና አፈፃፀም ወቅት ወጪ ሊቀንስ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶችን በአስተማማኝ መልክ ማቅረብ ናቸዉ። ለዚህም ትንሽ ወጪ አዉጥቶ ከፍተኛ ጠቀሜታ ማግኘት የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ የቅኝት መሣሪያዎችን ለመጠቀም መቻል ነዉ። ለአብነት ያህል የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች በሌሉበት ቦታ ወይም ተመሳሳይ የሆነ የመረጃ ክፍተት ባሉባቸዉ አካባቢዎች ጎጂ የአየር ሁኔታ ገፅታዎችን ለመከታተልም ሆነ፣ ከአየር ፀባይ ጋር የተያያዙ የልማት ዕቅዶች ለማዘጋጀት የሚቲዎሮሎጂ ሳተላይት መረጃ መቀበያ መሣሪያዎች መጠቀም የግድ ይሆናል።

እነኝህ የሳተላይት መረጃ መቀበያ መሣሪያዎች ዉድ ስለሆኑ፣ አብዛኛዉን ጊዜ፣ በብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ሥራ ላይ ዉለዉ የነበሩት በአለም አቀፍ ትብብር ከሚገኝ ርዳታ ሲሆን ከዚህ የሚገኙ መረጃዎች ለግብርና ለዉሀዉ እንዲሁም ለኮንስትራክሽን ሴክተሮች ለቅድሚያ ማስጠንቀቂያነት የሚሰጠዉን መረጃ ያጠናክራል።

በቀጣይነት በቅኝት መሣሪያነት ከፍተኛ ሚና ያለዉ ራዳር ሲሆን፣ከዉድነቱ የተነሳ እስካሁን የመሣሪያዉ ተጠቃሚ መሆን አልተቻለም። ዉሱን በሆኑ አካባቢዎች ላይ ለምሳሌ በኢኮኖሚና በኃይል ምንጭነት ጥቅም ላይ በዋሉ የወንዝ ተፋሰሶች ላይ ያለዉን የዕለት በዕለት የአየር ሁኔታ ክትትል ለማጠናከር ራዳር ምትክ የማይገኝለት የቅኝት መሳሪያ ሲሆን፣ በሰአታት ጊዜ ዉስጥ ከፍተኛ ጎርፍ ሊያስከትሉ የሚችሉ የክምር ደመና ስብስቦችን

ለመከታተል (በሳተላይት ሊታዩ የማይችሉ) ንብረትና ሕይወትን አድን ማስጠንቀቂያዎችን ለመስጠት የሚቻለዉ በራዳር አማካይነት ነዉ። በተጨማሪም የሚቲዎሮሎጂ ራዳር ለበረራ እና በአነስተኛ የቦታ እና የጊዜ ሽፋን የሚሰጡ የአየር ሁኔታ ትንበያዎች መሻሻል ከፍተኛ እገዛ ይሰጣል። በቅርቡ በተደረገ የጣቢያዎች አውታር ስርጭት ማስተር ፕላን መሰረት የአገሪቱን የቆዳ ስፋት ለመሸፈን እስከ 5 የሚደርሱ የራዳር ተከላዎች ያስፈልጋሉ። ከፍተኛ መዋዕለነዋይና ቴክኒካዊ አቅም ከማስፈለጉ አንፃር የአገሪቷ የቆዳ ሽፋን ሙሉ በሙሉ በራዳር ቅኝት ስር ለማድረግ ባይቻልም የአየር ሁኔታና ጠባይን የቅርብ ክትትል በሚያስፈልግበት አካባቢ የራዳር ሥራን ማስጀመር ተገቢ ነዉ።

በአጠቃላይ ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ከሚንቀሳቀስበት ዉጫዊ ሁኔታ (Macro environment) በርካታ አመቺ ሁኔታዎች ያሉት በመሆኑ እነዚህን ለአገልግሎቱ መጎልበት መጠቀም አስፈላጊ ነዉ።

## 7.2 የኤጀንሲው ዉስጣዊ ሁኔታዎች ትንተና

### 7.2.1. ጠንካራ ጎኖች

- ኤጀንሲው እንደ ዉሃ፣ ሀይል፣ ግንባታና ዲዛይን፣ ግብርና፣ ጤና፣ አየር ትራንስፖርት ኢንቨስትመንትና የተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፎች በግብዓትነት ሊያገለግሉ የሚችሉ የረጅም ጊዜ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች በማቅረብና የአጭርና የረጅም ጊዜ የአየር ሁኔታ ትንበያ በመስጠት ለዘርፎቹ ምርታማነትና ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችና አደጋዎችን ለመከላከል የጎላ አስተዋፅኦ ማድረግ ችሏል።
- ኤጀንሲው የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በድረ ገጽ በማቅረብ ሰፋ ላለ ተጠቃሚዎች እያሰራጨ ይገኛል።
- የአገሪቱን የአየር ሁኔታና ጠባይ ለመከታተል እና ለመተንበይ የሚያስችሉ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች አይነት፣ ብዛት እና ስርጭት ማስተር ፕላን አጥንቶ የጣቢያዎች ኔትወርክ ስርጭት እየተገበረ ነዉ ።

- የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት በክልሎች ለማስፋፋት የቅ/ጽ/ቤቶችን በማጠናከር ባለፉት 3 ዓመታት ብቻ እስከ 271 የሚደርሱ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው አዳዲስ ተጨማሪ ጣቢያዎችን በማቋቋም የተለያዩ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ይገኛል።
- የሚቲዎሮሎጂ መረጃን ለተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እቅዶችና ክንውኖች እንዲውል በመደረጉ የኤጀንሲው የአገልግሎት አድማስ እየተስፋፋ መጥቷል ።
- ለህብረተሰቡ በቅርበት የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል በሀገሪቱ የተለያዩ ክልሎች የአገልግሎት አድማሱን ለማዳረስ የቅርንጫፍ ፅ/ቤቶችና የተለያየ ደረጃ ያላቸዉ ጣቢያዎች በማቋቋም አገልግሎት መስጠት ተጀምሯል፤
- አህጉራዊና አለም አቀፋዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ልዉዉጥ ግዴታን በአግባቡ መወጣቱ ኤጀንሲው በመስኩ በስልጠናና ሙያዉን ሊያግዙ የሚችሉ የተለያዩ ድጋፎች እንዲሁም ተቀባይነትን በዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ደረጃ ለማግኘት አስችሎታል።

### 7.2.2 ደካማ ጎኖች

- ለሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ማሰባሰቢያ፣ ማጠናቀሪያና ማከማቻ የሚዉሉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን የመጠቀም አቅም አለመኖር ኤጀንሲው የሰዉ ጉልበት ላይ ብቻ እንዲወሰንና ወቅታዊ ሰፊ ሽፋንና አስተማማኝ (በአውቶማቲክ መሳሪያዎች የሚሰበሰቡ)መረጃ ለመስጠት ተፅዕኖ አሳድሯል።
- ከሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የሚገኝ ገቢን ለማሳደግ በሰፊዉ አለመሰራቱ ከአገልግሎቱ የሚገኘዉን ገቢ ዉስን አድርጎታል።
- የተጠናከረ የሰለጠነና የተደራጀ የሰው ኃይል አለመኖር፤ በዕርዳታ የሚካሄዱትን ፕሮጀክቶች የክትትል ስርዐት አለመለወጥ፤ የንብረት አስተዳደርና የውስጥ ቁጥጥር እና የማህደር አገልግሎት በዘመናዊ አሠራር አለመተካት።
- ኤጀንሲው ለዘመናት የሰበሰባቸው መረጃዎች ወደ ኮምፒዩተር ገብተው አለመደራጀታቸው፡፡
- ቅ/ጽ/ቤቶች በየክልል መንግስታት የተቋቋሙ ቢሆንም ከባለሙያዎች የልምድ ማነስ እና የፋሲሊቲዎች አለመሟላት ምክንያት የሚፈለግባቸውን አገልግሎት መስጠት አልቻሉም።
- ቅ/ጽ/ቤቶች መረጃ የሚያደራጁበት ዘመናዊ የመረጃ ቋት እንዲሁም መረጃ ለመለዋወጥ የሚረዳቸው ብሮድባንድ ኢንተርኔትም ሆነ የኮምፒዩተር መረብ አለመኖር፤

- በኤጀንሲው ውስጥ ወይንም በውጭ ሀገር በመለስተኛ የትምህርት ዘርፍ ሰልጥነው ሙያቸው በመንግሥት ዘንድ እውቅና አለማግኘታቸው በባለሙያዎች ዘንድ የሞራል ውድቀት በሥራው ላይ የጥራት ጉድለት አስከትሏል።
- ኤጀንሲው የተቋቋመበት አዋጅ ውስጥ የተካተቱ ተግባራት ከሌሎች መ/ቤቶች ኃላፊነት ጋር መደራረብ፤
- በኤጀንሲዉ የሴቶች በሁሉም መስክ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ አለመሆን እና የኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታን ለመዋጋት በቁርጠኝነት ያለመነሳት ናቸው፡፡

# 8. የኤጀንሲው ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች

በኤጀንሲው ዉስጣዊና ዉጫዊ ሁኔታዎች ቅኝትና የባለድርሻዎች ትንተና በተገኘዉ ዉጤት መሰረት የኤጀንሲው አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል ትኩረት የሚሹ ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች ተለይተዉ እንደሚከተለዉ ቀርበዋል።

## 8.1. መሰረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አቅርቦት አገልግሎትን በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ አለመቻል

- የሚቲዎሮሎጂ ምዝገባ ሳይንስ (meteorological observation) ጥቅም በሰፊዉ ባለመታወቁ ከመንግሥት ዉጭ ባለዉ የግል ኢኮኖሚ መስክ ሆነ በቀረዉ ሕብረተሰብ ዘንድ ትርጉም ያለዉ ጣቢያን በማቋቋም የመጠቀም ተሳትፎ አናሳ መሆን፣
- የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ስርጭት ለማሳደግ ከሚያስከትለዉ ወጭ አንፃር ያለዉ የአቅም ችግር፣
- የተቋቋሙ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ለመጠበቅ ከአካባቢዉ ህብረተሰብ የሚጠበቀዉ የዜግነት ግዴታ ከግንዛቤ ጉድለት ሳቢያ አለመታወቁ፣
- Automatic weather station የመጠቀም አቅም አናሳ መሆን፣
- ከአንዳንድ ጣቢያዎች የሚሰበሰቡ የሚቲዎሮጂ መረጃዎች ጥራት ማነስ፣

- በርካታ ጣቢያዎች ደረጃቸውን ጠብቀው በመረጃ ዓይነት የተሟላ እና በጊዜ ሽፋንም ያልተቆራረጠ መረጃ እንዲልኩ ለማድረግ ያለው የሰው ኃይል እና የማቴሪያል አቅም ውሱንነት፣
- በዓለም አቀፍና በሀገር ውስጥ ያሉ የመገናኛ መስመር የአቅም ዉስንነት ከቅ/ጽ/ቤ/ቶች ጋር የመረጃ ልውውጥ ለማድረግም ሆነ በትንበያ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች አሟልቶ መቀበል አለመቻል፣
- ከየጣቢያዎች የሚሰበሰቡ መረጃዎች በየጊዜዉ ተጠናቅረዉ ተጠቃሚዎች በሚፈልጉት አገልግሎት ላይ ሊዉሉ በሚችሉበት ደረጃ አለመገኘት፣
- የመረጃ መሰብሰቢያና ማጠናቀሪያ መሳሪያዎች አለመሟላት፣
- በብዙ ጣቢያዎች መረጃ የሚሰበስቡ ባለሙያዎች ቅጥር ጊዜያዊ መሆኑና ለመረጃው ጥራት የሚሰጡት ትኩረት አናሳ መሆን፣
- ለኢንስፔክሽን የሚላኩ ባለሙያዎች ጥቃቅን የመሣሪያ ጥገና የማድረግ አቅም ውሱንነት፣
- የጣቢያዎች መረጃ ያልተሟላና የተሳሳተ መሆን (Latitude, Longitude, Altitude and other station **information**) ወጥነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ የጂ አይ ኤስ ትንተና መስጠት አለመቻል፣
- እንደ የአየር ግፊትና ንፋስ ፍጥነት መለኪያ መሣሪያዎች ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- መረጃ ለሚሰበስቡ ባለሙያዎች በዕቅድ የሚመራ፤ የተጠናና ተከታታይ የተሀድሶ ስልጠና ስልት አለመኖር።

**መሰረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አቅርቦት አገልግትን በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ አለመቻል ትኩረት ካልተሰጠዉ የሚከተሉትን ተጽዕኖዎች እንደሚያስከትል ይገመታል**

- ያልተሟላ የአገልግሎት አሰጣጥን ማስከተል፣
- ለተጠቃሚዎች በሚፈልጉት አካባቢ በቅርበት (Area Specific) የአገልግሎት መሰጠት አለመቻል፣
- በአየር ሁኔታ ገፅታዎች ላይ የቅርብ ክትትል ባለማድረግ የተነሳ በህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ፣

- ያልተሟላ፣ ደረጃውን ያልጠበቀ፣ የተቆራረጠ፣የሀገሪቱን የቆዳ ሽፋን ያላገናዘበ መረጃ መኖር፣
- ለአገሪቱ እድገት በቂ ድጋፍ መስጠት የተሳነው የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ማሰባሰብ፣
- በአየር ሁኔታ ገፅታዎች ላይ የቅርብ ክትትል ባለማድረግ የተነሳ በህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ፣
- ዓለም አቀፍ ገፅታዎችን መወጣት አለመቻል ብሎም ከዓለም አቀፍ የመረጃ ኔትወርክ መዉጣትን፣
- ባልተሟላ መረጃዎች ላይ በመመስረት የሚሰጥ አገልግሎት በተጠቃሚዎች ዘንድ ተአማኒነትን ማሳጣት ደንበኞች ሌሎች አማራጮችን እንዲፈልጉ ማድረግን፣
- ለተጠቃሚዎች በወቅቱ የመረጃ አገልግሎት መስጠትና በመረጃ ጥራት ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለማስተካከል አለመቻልን፣
- ተጠቃሚዎች በሚፈልጉት የአገልግሎት ዘርፍ ተገቢዉን አገልግሎትና ምክር መስጠት አለመቻልን።
- የሚቲዎሮሎጂ ልዩ ልዩ ዘርፎች ካላቸዉ ተፈላጊነት አንጻር ባለሙያዎች ወደሌላ ድርጅት መፍለስ፣
- በኮምፐዩተር ሳይንስ፣ በኤሌክትሮኒክስ ኮሙኒኬሽን ፣ ምህንድስና እና ሌሎች ቁልፍ የሙያ ዘርፍ ልምድ ያለው እና በመንግሥት የደምወዝ ክፍያ የሚሠራ ባለሙያ ከገበያ ማጣት፣
- በኤጀንሲው የሚሰጡ ስልጠናዎች እውቅና አለማግኘት በጣቢያዎች ላይ የሚሠሩ ሠራተኞች መፍለስ፣
- በፍጥነት የሚያድጉ ቴክኖሎጂዎችን ለማወቅና ለመጠቀም በበቂ የጥራት ደረጃና መጠን እንዲሰለጥኑ አለማድረግ፣
- ባለሙያዎች እድገት ካገኙበት የሥራ መደብ ውጭ መሥራት፣
- አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ በሚቲዎሮሎጂ የሙያ ዘርፍ በዲፕሎማ ደረጃ ይሰጥ የነበረውን ሥልጠና መቋረጡ፣
- አዳዲስ የትምህርት ፖሊሲዎች መቀረጽ፣

- ለዘመናዊ ለዉጥ ባይተዋር መሆን፣
- የአገልግሎት መስተጓጎልና መቋረጥ፣
- ልምድ የሌላቸው ባለሙያዎችን ለአጭር ጊዜ ልምድ አግኝተው እስኪለቁ ድረስ ብቻ በመጠቀም የሥራዎች ቀጣይነት እና ወጥነት አደጋ ላይ መውደቅ፣
- ተጠቃሚዎች በሚፈልጉት የአገልግሎት ዘርፍ ተፈላጊዉን አገልግሎትና ምክር መስጠት አለመቻል፣
- ኤጀንሲው ከሚቲዎሮሎጂ መስክ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት መወጣት አለመቻል።

## 8.2 የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን በዋናዉ መ/ቤት፣ በቅ/ጽ/ቤቶች እና በጣቢያዎች አጠናክሮ ለመስጠት የሚያስችል አቅም ውስን መሆን

- የተደራጀ ዘመናዊ መሳሪያ እና በቢሮ አለመሟላት
- በጥራት መረጃዎች አለመሰብሰብና የተሸከርካሪ እጥረት
- በየቅ/ጽ/ቤቶች መሳሪያዎችን ለመጠገን የሚያስችል የካሊቢረሬሽንና ጥገና ለማድረግ የሚያስችል የካሊብሬሽንና የጥገና ላብራቶሪ አለመኖር ፣
- በየጣቢያዉ መሳሪያዎችን ለመጠገን ስልጠና የሚሰጡ ባለሙያዎች አለመኖር፣
- የሚሰበሰቡ የሚቲዎሮሎጂጂ መረጃዎች በቀለላሉ ለተጠቀቃሚ ተደራሽ አለመሆን ፣
- ቀልጣፋ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አቅምና ስርዓት አለመኖር

## የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን በዋናዉ መ/ቤት ፣ በቅ/ጽ/ቤቶች እና በጣቢያዎች አጠናክሮ ለመስጠት የሚያስችል አቅም ውስን መሆን የሚያስከትለዉ ተጽዕኖዎች

- ጥራትና ብቃት ያለዉ መረጃ አለማግኘት ፣
- በዘመናዊ መሳሪያዎች ካለመኖር የተነሳ ቅ/ጽ/ቤቶች በማዕከል መረጃ መለዋወጥ መስተጓጎል

- ብቃት ያለዉ የሰለጠነ ቴክኒሺያን አለመኖር ፣ በዉድ እና በዉጭ ምንዛሪ የሚገዙ መሳሪያዎች ያለጥቅም መቀመጥ ፣

## 8.3. ወቅታዊና ጥራታቸውን የጠበቁ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶችን ለመስጠት አለመቻል

- በኤጀንሲው የጥናትና ምርምር ሥራ የሚመራበት የአሰራር ስርዓት (የጥናትና ምርምር ፖሊሲ) ተግባራዊ አለመሆን ፣
- የቅንጅታዊ ሥራ ባለመኖሩ የኤጀንሲውን ችግር ሊፈታ የሚችል ጥናትና ምርምር አለመኖር፣
- ገበረሬዉ ማዕከል ያደረገ በቂ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት አለመኖር፣
- በሚቲዎሮሎጂ ዘርፍ በአገሪቱ ላይ የተሠሩ የጥናትና ምርምርም ውጤቶች በአቅም ዉስንነት የተነሳ ማሰባሰብ፤ ማሳተምና ማሰራጨት አለመቻሉ፣
- የጥናትና ምርምር ሥራዎች እውቅና ያገኘና ለኤጀንሲው አገልግሎት ማሻሻያ አስተዋፅኦ ላደረጉ የጥናትና ምርምር ውጤት ባለቤቶች የማበረታቻ ሥርዓት አለመኖር፣
- ለኤጀንሲው አገልግሎት ድጋፍ የሚሰጡ ጥናትና ምርምሮች ትኩረት አለመሰጠቱ፣
- የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ገምግሞ ለህትመት የሚያበቃ አካል አለመኖር፣
- በከባቢ አየር ዉስጥ ለበረራ አስጊ የሆኑ ክስተቶችን ለመከተታተል የICAO መስፈርት የማሟላት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ የሚችል Watch office አለመሟላት
- ደረጃዉን የጠበቀ አስተማማኝ መረጃ እና ትንበያ ለተጠቃሚዎች በቅርበት አለማድረስ፣
- የቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ አቅም የተዋቀሩበትን አላማ ለመወጣት አለመቻል ፣
- በግብርና ሚቲዎሮሎጂ ዘርፍ አቅጣጫ ምርታማ አለመሆን ፣

**ወቅታዊና ጥራታቸውን የጠበቁ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶችን ለመስጠት ካልተቻለ የሚከተሉትን ተጽዕኖዎች ያሳድራል ፡**

- የኤጀንሲውን ኦፕሬሽናልና ልማት ሥራዎችን ሊያሻሽሉ የሚችሉ የምርምር ዉጤቶች አለመገኘት፣
- በአንድ ጉዳይ ላይ ተደጋጋሚ ሥራዎች/ጥናቶች እንዲሰሩ ማድረግ፣

በኤጀንሲው የሚከናወኑ የጥናትና የምርምር ዉጤቶችን በአግባቡ አለመያዝ እና የምርምር ሥራዎች ባለቤት ማጣት፣

## 8.4 ሕብረተሰቡ ስለሚቲዎሮሎጂ ሣይንስና አገልግሎት ያለዉ ግንዛቤ አለመዳበር ፤

- የአየር ትንበያ በመገናኛ ብዙኃን ማቅረብ ሥራ ላይ የሰለጠነ ባለሙያ እጥረት ፤
- ስለ ሚቲዎሮሎጂ ሳይንስ መሠረታዊ ዕውቀትን የሚያስጨብጡ ጽሑፎች በበቂ ሁኔታ አለመኖር
- በመስኩ በቂ የአህዘቦት ሥራ አለመሰራትና ችግሩን ለማስወገድ የጥናትና ምርምር ሥራ ያለመካሄድ፣
- በኤጀንሲዉና በተጠቃሚዉ ማህበረሰብ እንዲሁም ከተባባሪ አካላት ጋር ጠንካራ ግንኙነት አለመኖር

**የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስና አገልግሎት ጠቀሜታ በሕብረተሰቡ ዘንድ የበለጠ ግንዛቤ እንዲያገኝ ካልተደረገ የሚያስከትለዉ ተጽዕኖ ፤**

- የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መስፋፋት አለመቻልን እንዲሁም ህብረተሰቡ የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያ ተጠቃሚ አለመሆንን፣
- ህብረተሰቡ ልማዳዊ አሰራርን መከተል፣
- በሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ በማሳደር ፈጣን እድገት እንዳይመጣ ማድረግ
- ከተባበባሪ አካላት ጋር ጠንከካራ ግንኙነት በባለመኖረሩ ማግኘት የሚገባዉን ድጋፍ ማነስ፣

## 9 ወሳኝ የሆኑ ስልታዊ ጉዳዮች ምዝና

1. ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ጉዳዮች
2. በአስቸኳይ እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገበባ ጉዳዮች
3. ከኤጀንሲው እሴቶች ጋር ከፍተኛ ቀረቤታ ያላቸው ጉዳዮች

| ተራ ቁጥር | ወሳኝ ጉዳቶች | 1 | 2 | 3 |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መሰረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አቅርቦት አገልግትን በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ አለመቻል | x | x | x |
| 2 | የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን በዋናዉ መ/ቤት፣ በቅ/ጽ/ቤቶች እና በጣቢያዎች አጠናክሮ ለመስጠት የሚያስችል አቅም ውስን መሆን | x | x | x |
| 3 | ወቅታዊና ጥራታቸውን የጠበቁ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶችን ለመስጠት አቅም ውስን መሆን | x | x | x |
| 4 | ህብረተሰቡ ስለሚቲዎሮሎጂ ሳይንስና አገልግሎት ያለዉ ግንዛቤ አለመዳበር | x | x | x |

## 10. አማራጭ ስትራቴጂዎች እቅድ

### 10.1 መሰረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አቅርቦት አገልግትን በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ አለመቻል

10.1.1 መሰረታዊ ሚቲዎሮለሎጂ መረጃ አቅርቦት አገልግሎትን በሚያረካ ደረጃ ለማቅረብ ዘመናዊ መሳሪያወዎችን መጠቀም፣

10.2 የሚቲዎሮሎጂ መረጃ በቦታ፣ በጊዜና በበቂ ሽፋን አሚልቶ መሰብሰብና የሚሰበሰቡትን መረጃዎች ጥራትና ተከታታይነት እንዲኖራቸዉ የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት ፣

### 10.2 የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን በዋናዉ መ/ቤት፣ በቅ/ጽ/ቤቶች እና በጣቢያዎች አጠናክሮ ለመስጠት የሚያስችል አቅም ውስን መሆን

10.2.1 የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ለተጠቃሚዎች በቅርበት ለማዳረስ የቅ/ጽ/ቤቶችን የአቅም መገንባት

10.2.2 የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ለማሻሻል በተጠቃሚዎች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማካሄድ

### 10.3. ወቅታዊና ጥራታቸውን የጠበቁ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶችን ለመስጠት አቅም ውስን መሆን

10.3.1 አቅምን በመገንባት የጥናትና ምርምር፣ የትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማሻሻል፣

10.3.2 የኤጀንሲዉን የጥናትና ምርምር፣ የትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እንዲሁም የግብርና ሚቲዎሮሎጂን የአቅም መገንባት

### 10.4 የህዝቡን የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስና አገልግሎት ግንዛቤ ለማሳደግ የህዝብ ግንኙነት ፕሮግራም ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፣

10.4.1 የህዝቡን የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስና አገልግሎት ግንዛቤ ለማሳደግ የህ/ግ/ፕሮግራም ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ

10.4.2 የሚቲዎሮሎጂ የህዝብ ግንኙነት ስራን በኤጀንሲዉ ባለሙያዎች በስፋት መስጠት

## 11. ወሳኝ ጉዳዮች ላይ የቀረቡ አማራጭ ስትራቴጂዎች ምዘና

| መለኪያ | ነጥብ |
|---|---|
| ከፍተኛ | 3 |
| መካከለኛ_ | 2 |
| ዝቅተኛ | 1 |
| ተቀባይነት የማይኖረው_ | 0 |

### 11.1. ስትራቴጂያዊ ጉዳይ- መሠረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አቅርቦት አገልግሎትን በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ

| ተቁ | አማራጭ ስትራቴጂዎች | ኢኮኖሚያዊ | ህጋዊ | ፖሊቲካዊ | ማህበራዊ | ቴክኒካዊ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መሠረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አቅርቦት አገልግሎትን በሚያረካ ደረጃ ለማቅረብ ዘመናዊ መሳሪያዎችን መጠቀም | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 14 |
| 2 | የሚቲዎሮሎጂ መረጃ በቦታ በጊዜና በበቂ ሽፋን አሟልቶ መሰብሰብና የሚሰበስቡትን መረጃዎች ጥራትና ተከታታይነት እንዲኖራቸዉ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 12 |

### 11.2 የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን በዋናዉ መ/ቤት በቅ/ጽ/ቤቶች እና በጣቢያዎች አጠናክሮ ለመስጠት የሚያስችል አቅም ውስን መሆን፣

| ተቁ | አማራጭ ስትራቴጂዎች | ኢኮኖሚያዊ | ህጋዊ | ፖሊቲካዊ | ማህበራዊ | ቴክኒካዊ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ለተጠቃሚዎች በቅርበት ለማዳረስ የቅ/ጽ/ቤቶችን የአቅም መገንባት | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 14 |
| 2 | የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ለማሻሻል በተጠቃሚዎች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማካሄድ | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 14 |

11.3. <u>ወቅታዊና ጥራታቸውን የጠበቁ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶችን ለመስጠት አለመቻል</u>

| ተቁ | አማራጭ ስትራቴጂዎች | ኢኮኖሚያዊ | ህጋዊ | ፖሊቲካዊ | ማህበራዊ | ቴክኒካዊ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የኤጀንሲዉን የጥናትና ምርምር፣ የትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እንዲሁም የግብርና ሚቲዎሮሎጂን የአቅም መገንባት | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 15 |
| 2 | አቅምን በመገንባት የጥናትና ምርምር የትንበያና ቅድመ ማስጠንቀቂያና የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማሻሻል | 3 | 3 | 3 | 3 | 5 | 20 |

11.4. <u>ህብረተሰቡ ስለሚቲዎሮሎጂ ሳይንስና አገልግሎት ያለዉ ግንዛቤ አለመዳበር ፤</u>

| ተቁ | አማራጭ ስትራቴጂዎች | ኢኮኖሚያዊ | ህጋዊ | ፖሊቲካዊ | ማህበራዊ | ቴክኒካዊ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የህዝቡን የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስና አገልግሎት ግንዛቤ ለማሳደግ የህ/ግ/ፕሮግራም ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ | 2 | 3 | 5 | 3 | 5 | 18 |
| 2 | የሚቲዎሮሎጂ የህዝብ ግንኙነት ስራን በኤጀንሲዉ ባለሙያዎች በስፋት መስጠት | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 25 |

# 12 ስትራቴጂክ መርሀ ግብር

| ስትራቴጂክ ጉዳይ | መወሰድ የሚገባው እርምጃ | አስፈጻሚ አካል | የጊዜ ሰሌዳ | | | | | ለስራው የሚያስፈልገው የወጪ ግምት በሺህ ብር | የፋይናንስ ምንጭ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 03 | 04 | 05 | 06 | 07 | | ከመንግስት | ከእርዳታ |
| መሠረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አቅርቦት አገልግሎትን በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ | የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎችን ሽፋን ማሳደግ፣ | የኤሌክትሮኒክ ጣቢያዎች እና የICT ዳይሬክተር | X | X | X | X | X | | | |
| | • Radar Station | “” | | | X | X | | 10,000 | | |
| | • AWOS Stations | “” | | X | X | | | 5,000 | | |
| | • DWS Stations | “” | X | X | X | | | 9,400 | | |
| | • AWS Station | “” | X | X | X | X | X | 30,000 | | 175 |
| | • Satellite Rceiving Stations | “” | | | X | X | X | 5,500 | | 80 |
| | • Upper Air Stations | “” | X | X | X | | | 12,000 | | |
| | • Airpolution Stations | “” | X | X | X | | | 3,300 | | |
| | ታሪካዊ መረጃወዎችን ማደራጀት (Data Rescue) | መሰረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ እና ክላይማተቶለሎጂ ዳይሬክተር | X | X | X | | | | | 2,192 |
| | • ዘመናዊ የመረጃ ቋት ማልማት (CDBMS) | “” | X | X | X | | | 2,600 | | |
| | • የጣቢያ ታሪካዊ መረጃ ማደራጀት (Metadata) | “” | | X | | X | | 120 | | |

| ስትራቴጂክ ጉዳይ | መወሰድ የሚገባዉ እርምጃ | አስፈጻሚ አካል | የጊዜ ሰሌዳ | | | | | ለስራው የሚያስፈልገው የወጪ ግምት (በሺህ ብር) | የፋይናንስ ምንጭ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 03 | 04 | 05 | 06 | 07 | | ከመንግስት | ከእርዳታ |
| | • የመረጃ ፖሊሲን አሻሽሎ ማዉጣት | መሰረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ እና ክላይማቶሎጂ ዳይሬክቶሬት | | X | | | | 120 | | |
| | • የሳተላይት መረጃዎችን ለመጠቀም የሚያስችል አቅም መገንባት | “” | | X | X | | | 2,000 | | |
| | • የመረጃ ጥራት ቁጥጥር ማኑዋል ማዘጋጀት | “” | | X | X | | | 100 | | |
| | የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች የካልብሬሽን እና ጥገና ላብራቶሪ መገንባት | ኤሌክትሮኒክ ጣቢያዎች እና የICT ዳይሬክተር | | | X | X | | 2,500 | | |
| | የጣቢያዎችን ቅኝት አቅም መገንባት፣ | “” | X | X | X | X | X | 12,743 | | |
| | • የመረጃ ማጠናቀር እና የክላይቶሎጂ አገልገሎትን ማጠናከር | መሰረተታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ እና ክላይማቶሎጂ ዳይሬክተር | X | X | X | X | X | 600 | | |
| | ወቅታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን በማዕከል በማሰባሰብ በአርካይቭ እና መረጃ ቋት ማደራጀት፣ ማስተዳደር፣ የጥራት ቁጥጥር ማካሄድ፣ ደህንነታቸዉን ማረጋገጥ፣ ማጠናቀር፣ መተንተን እና ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት | “” | X | X | X | X | X | 500 | | |
| | Establishment of Conventional Meteorological Stations | | | | | | | 6,993.3 | | |

| ስትራቴጂክ ጉዳይ | መወሰድ የሚገባዉ እርምጃ | አስፈጻሚ አካል | የጊዜ ሰሌዳ | | | | | ለስራዉ የሚያስፈልገዉ በ/000/ ብር | የፋይናንስ ምንጭ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 03 | 04 | 05 | 06 | 07 | የወጪ ግምት (በሺህ ብር) | ከመንግስት | ከእርዳታ |
| የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን በዋናዉ መ/ቤት በቅ/ጽ/ቤቶች እና በጣቢያዎች አጠናክሮ ለመስጠት የሚያስችል አቅም ዉስን መሆን፣ | **የህንጻ ግንባታ**<br>• የ50 የዐብይ ጣቢያ ቢሮዎች ግንባታ ማካሄድ (2004-2007)<br>• የዋና መ/ቤትና የጥናት፣ ምርምርና የስልጠና ማዕከል ሰባት ህንጻዎች እድሳትና ጥገና ማከናወን (2004-2005) | ኤሌክትሮነኒክ ጣቢያዎች እና የICT ዳይሬክተር | X | X | X | X | X | 62,500 | | |
| | • በአራት ቅርንጫፈ ጽ/ቤቶች የአጥር ግንባታ ማካሄድ (2004-2006) | “” | X | X | X | X | X | | | |
| | • በሁለት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የካፊቴሪያ ግንባታና የሳይት ወርክ ማካሄድ (2005-2006) | “” | X | X | X | X | X | | | |
| | • በ7 ቅርንጫፍ ጸ/ቤቶች የጀነሬተር ህናጻ ግንባታ ማካሄድ (2004-2007) | “” | X | X | X | X | X | | | |
| | • በአስራ አንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የህንጻ እድሳትና ጥገና ማካሄድ (2004-2006) | “” | X | X | X | X | X | | | |
| | • 75 የዐብይ ጣቢያ ቢሮዎች እድሳትና ጥገና ማካሄድ (2004-2007) | “” | X | X | X | X | X | | | |
| | • የመገናኛ አዉታር ማጠናከር | “” | X | X | X | X | X | | | |
| | • የአዉቶሜሽን ስራዎች መተግበር | “” | X | X | X | X | X | | | |
| | • የአይ ሲ ቲ ፖሊሲ እና የአደጋ መከላከል ዕቅድ | “” | | X | | X | | | | |
| | • ድረ-ገጽ ዘመናዊ ማድረግ | “” | X | | | | X | | | |
| | • የጂ አይ ኤስ አቅም ማሳደግ | “” | | X | X | | | | | |

| ስትራቴጂክ ጉዳይ | መወሰድ የሚገባዉ እርምጃ | አስፈጻሚ አካል | የጊዜ ሰሌዳ | | | | | ለስራዉ የሚያስፈልገዉ | የፋይናንስ ምንጭ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 03 | 04 | 05 | 06 | 07 | የወጪ ግምት (በሺህ ብር) | ከመንግስት | ከእርዳታ |
| | ከአዲስ አበባ ናይሮቢ ያለዉን Regional Telecommunication HUB እንዲጀምር ማድረግ | ኤሌክትሮኒኒክ ጣቢያዎች እና የICT ዳይሬክተር | X | X | | | | 3,000 | | |
| | ከሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች በቀጥታ መረጃ ለማሰባሰብ የሚያስችል ስርዓት ማደራጀት (In country network Development) | “” | | X | X | | | 70,000 | | |
| | V-sat Network connection of 8 Airports | “” | | X | X | | | 5,000 | | |
| | | “” | | | | | | | | |
| | በዋና መ/ቤት የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች ማምረቻ ህንጻና ተጨማሪ ህንጻ ግንባታ ማከናወን ፡(2004-2005) | “” | | | | | | | | |
| | ስቱዲዮ ማቋቋም (ሁለት)<br>• አንድ አዲስ<br>• አንድ ማጠናከር | | | | | | | 1,000,500 | | |

| ስትራቴጂክ ጉዳይ | መወሰድ የሚገባዉ እርምጃ | አስፈጻሚ አካል | የጊዜ ሰሌዳ | | | | | ለስራዉ የሚያስፈልገዉ | የፋይናንስ ምንጭ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 03 | 04 | 05 | 06 | 07 | የወጪ ግምት (በሺህ ብር) | ከመንግስት | ከእርዳታ |
| ወቅታዊና ጥራታቸውን የጠበቁ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶችን ለመስጠት አለመቻል | ወቅታዊ የሆኑ፣ ጥራታቸዉን የጠበቁና በአይነት የበዙ ለኤጀንሲዉ ኦፕሬሽናል ስራ የሚረዱ የምርምር ስራዎች፣ ጥናትና ምርምሮችን ማስተባበር እና ማካሄድ<br>• በግብርና በHydrology Climate Change etc..... | የሚቲዎሮሎጂ እና ተዛማጅ የሳይንስ ዘርፎች ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት | x | x | X | x | x | 56,000.00 | | |
| | • በኦዞን ስምምነቶች ዉስጥ የተካተቱ ግዴታዎችንና ሀላፊነቶችን በፍጥነትና በጥራት በማሟላት ኦዞንን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን በአማራጭ ኬሚካሎችና ቴክኖሎጂዎች መተካት | “” | x | x | X | x | x | | | |

| ስትራቴጂክ ጉዳይ | መወሰድ የሚገባዉ እርምጃ | አስፈጻሚ አካል | የጊዜ ሰሌዳ | | | | | ለስራዉ የሚያስፈልገዉ | የፋይናንስ ምንጭ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 03 | 04 | 05 | 06 | 07 | የወጪ ግምት (በሺ.ህ ብር) | ከመንግስት | ከእርዳታ |
| | የአጭር ጊዜ አሀዛዊ ትንበያን ወረዳ ተኮር ለማድረግ የሚያስችል አቅም ግንባታ ማካሄድ | የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ዳይሬክቶሬት | X | X | X | X | X | 70,000.00 | | |
| | ዳይናሚካል ሞዴሎችን መሰረት ያደረጉ ወቅታዊና የረዥም ጊዜ ትንበያዎችን መጀመር | “ | X | X | X | X | X | | | |
| | የየአካባቢውን አግሮ ክላይሜቲክ መረጃዎችን በማጠናቀር የእርሻ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን ቅድመ ማስጠንቀቂያዎችን ትንበያዎችንና ሪስፖንስ ፋርሚንግ አገልግሎትን መስጠት | የልማት ሚቲዎሮሎጂ ዳይሬክቶሬት | | | | | | 80,000.00 | | |
| | ለሪስፖንስ ፋርሚንግ የሚውል ማኑዋል ማዘጋጀትና መረጃዋችንና ትንብያዎችን ለግብርና ሚ/ር የልማት ሠራተኞችና በየጠቋሚ ጣቢያዎች ባሉ ሠራተኞች ስልጠና መስጠት | “ | X | X | X | X | X | | | |
| | ለዉሀና ኢነርጅ ተኮር የHydro meteorology ትንበያና የምክር አገልግሎት ተግባራዊ ማድረግ | “ | X | X | X | X | X | | | |
| | ለወባ ለማጅራት ገትርና የአተት ወረርሽኝን ቀድሞ ለመከላከል የሚያስችል የጤና ሚቲዎሮሎጂ ትንበያና የምክር አገልግሎትን ተግባራዊ ማድረግ ፣ | “ | X | X | X | X | X | | | |
| | የአቪየሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ዘመኑ በሚጠይቃቸዉ የቴክኖሎጂ አሰራሮች መሰረት ያደረገ ለዉጥን መተግበር | የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት | X | X | X | X | X | 90,000.00 | | |
| ህብረተሰቡ ስለሚቲዎሮሎጂ ሳይንስ አገልግሎት ያለው ግንዛቤ አለመዳበር | የህዝቡን የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስና አገልግሎት ግንዛቤ ለማሳደግ የተጠናከረ የህዝብ ግንኙነት አገልግሎት ተግባራዊ ማድረግ | የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት | X | X | X | X | X | 5,000.00 | | |

| ስትራቴጂክ ጉዳይ | መወሰድ የሚገባዉ እርምጃ | አስፈጻሚ አካል | የጊዜ ሰሌዳ | | | | | ለስራዉ የሚያስፈልገዉ | የፋይናንስ ምንጭ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 03 | 04 | 05 | 06 | 07 | የወጪ ግምት (በሺህ ብር) | ከመንግስት | ከእርዳታ |
| | ተከታታይ ትምህርታዊ የሬዮና ቴሌቪዥን ፕሮግራም ዶክመንተሪ ፊልሞች፣ ግብረ መልስ፣ የዉይይት መድረግ፣ ሁነቶች ወዘተ ፣ በራሪ ጽሁፎች መጽሔቶች፣ ፕሬስ ሪሊዝ፣ ፕሬስ ኮንፍረንስ፣ ቃለ ምልልስ ወዘተ አዘጋጅቶ የተገልጋዩን ግንዛቤ ማዳበር ፣ | የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት | X | X | X | X | X | 2,000.00 | | |
| | የተለያዩ መልዕክቶችን በመቅረጽ የኤጀንሲዉን አቋም ለህብረተሰቡ በተከታታይ ማሳወቅ | “” | | | | | | 5500.00 | | |
| | መልካም የሚዲያ ግንኙነት በመፍጠር ወቅታዊ መረጃን ለህብረተሰቡ እንዲደርስ ማድረግ፣ እንዲሁም ኤጀንሲዉን በማስመልከት የሚዲያ ሞኒተሪንግ ስራ ማካሄድና ግብረ መልስ በመስጠት የተቋሙን መልካም ገጽታ ማጉላት | “” | | | | | | 2,500,000 | | |
| | የኤጀንሲዉን የስራ እንቅስቃሴ የሚያሳዩና አስተማሪ መልዕክቶችን በመጽሔት ዝግጅት፣ ብሮሼር፣ በራሪ ጽሁፎች፣ አርቲክሎች መጻፍና በተለያየ ሚዲያ ማሰራጨት (Broadcast, print and website) | “” | | | | | | 1,000,000 | | |
| | በተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የዉይይት መድረክ በማዘጋጀት በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ በመመካከር መግባባት በተቋሙ እንዲፈጠር ማድረግ፣ | “” | | | | | | 100,000 | | |
| | ኤጀንሲው በተመለከተ የቀውስ ጊዜ ግንኙነትን ማቀድና መምራት | “” | | | | | | 200,000 | | |
| | ኤጀንሲዉን መልካም ገጽታ በተለያየ ዘዴ ማስተዋወቅ (ሬዲዮ፣ የቲቪ ወዘተ የማስታወቂያ ስራ መስራት) | “” | | | | | | 200,000 | | |
| | ተከታታይ የተገልጋዮች የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤቱን መሰረት አድርጎ ኤጀንሲዉን ማማከር | “” | | | | | | 400,000 | | |

| ስትራቴጂክ ጉዳይ | መወሰድ የሚገባዉ እርምጃ | አስፈጻሚ አካል | የጊዜ ሰሌዳ | | | | | ለስራዉ የሚያስፈልገዉ | የፋይናንስ ምንጭ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 03 | 04 | 05 | 06 | 07 | የወጪ ግምት (በሺህ ብር) | ከመንግስት | ከእርዳታ |
| | የኤጀንሲዉ የሂሳብ አሰራር የመንግስትን የፋይናንስ ደንብና መመሪያ ተከትሎ መስራቱንና መዛግብቱ በወቅቱ ተመዝግበዉ መዘጋታቸዉን ሪፖርት ማቅረብ | የኦዲት ዳይሬክቶሬት | X | X | X | X | X | 5,000.00 | | |
| | የኤጀንሲዉ ንብረት አያያዝና አጠባበቅ እንዲሁም አጠቃቀም ለኤጀንሲዉ አገልግሎት በመንግስት የንብረት አጠባበቅ መሰረት ኢኮኖሚያዉ ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ስራ ላይ መዋሉን ግምገማ በመካሄድ ሪፖርት ማቅረብ | “” | X | X | X | X | X | | | |
| | የሰራተኛዉን የመረጃ ዳታ-ቤዝ በዘመናዊ መንገድ ማጠናከር (መገንባት) | የሰዉ ሀብት እና የጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት | X | X | X | X | X | 25,000.00 | | |
| | የኤጀንሲዉን ጥቅል የሰዉ ሀይል ማሟላት የሚችል የአቅም ግንባታ ማካሄድ | “” | X | X | X | X | X | | | |
| | የኤጀንሲዉን የሰዉ ሀይል ልማት (HRD) ፖሊሲ አጥንቶ ተግባራዊ ማድረግ ፣ | “” | X | X | X | X | X | | | |
| | ኤጀንሲዉን የሰለጠነ የሰዉ ሀይል እጥረት ለመቅረፍ የተለያየ ደረጃ ያላቸዉ መለስተኛ የሚቲዎሮሎጂ ባለሙያዎችን በዓለም ሚቲዎሮሎጂ የባለሙያ መሰላል መሰረት ማሰልጠን፣ | የስልጠና ዳይሬክቶሬት | | | | | | 521,000.00 | | |

| ስትራቴጂክ ጉዳይ | መወሰድ የሚገባዉ እርምጃ | አስፈጻሚ አካል | የጊዜ ሰሌዳ | | | | | ለስራዉ የሚያስፈልገዉ | የፋይናንስ ምንጭ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 03 | 04 | 05 | 06 | 07 | የወጪ ግምት (በሺህ ብር) | ከመንግስት | ከእርዳታ |
| | ኤጀንሲዉ የደንበኛን ፍላጎት ለማርካት የሚያስፈልጉ የሚቲዎሮሎጂ ባለሙያዎችን በተለያዩ ስፔሻላይዜሽን እና አጫጭር ስልጠናዎች በዉጭ ሀገርና በሀገር ዉስጥ እንዲሰለጥኑ ማድረግና ማስተባበር ፣ | “” | X | X | X | X | X | | | |
| | የኤጀንሲዉን የትራንስፖርት ስምሪት ዳታ ቤዝ በዘመናዊ መንገድ መገንባት፣ | “” | X | X | X | X | X | | | |
| | የኤጀንሲዉን ስትራቴጂ እና ተልዕኮ ለማሳካት በመ/ቤቱ አሰራር ዉስጥ እስትራቴጂ እና አፈጻጸም (Strategy and Operation) በሚገባ ተናበዉ የሚሄዱ መሆናቸዉን ማረጋገጥ፣ | የለዉጥ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት | X | X | X | X | X | 4,500.00 | | |
| | የፈጻሚ ቡድኖችን የሙያ ብቃት ማጎልበት እና የለዉጥ ሂደቱ ተግባራዊነት መከታተል፣ | | X | X | X | X | X | | | |
| | ኤጀንሲዉ የላቀ አፈጻጸም እና የተዋጣለት አገልግሎት ባለቤት ሆኖ እንዲቀጥል በመ/ቤቱ የአሰራር ለዉጡ እንዲቀጥል መስራት እና የለዉጥ ሀይል የማፍራት ስራ ማከናወን ፣ | | X | X | X | X | X | | | |

| ስትራቴጂክ ጉዳይ | መወሰድ የሚገባዉ እርምጃ | አስፈጻሚ አካል | የጊዜ ሰሌዳ | | | | | ለስራዉ የሚያስፈልገዉ | የፋይናንስ ምንጭ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 03 | 04 | 05 | 06 | 07 | የወጪ ግምት (በሺህ ብር) | ከመንግስት | ከእርዳታ |
| | የኤጀንሲዉን ንብረት አያያዝ ዳታ ቤዝ በዘመናዊ መልኩ ማጠናከር | የፋይናንስ ግዥና ንብረት አስተዳደር | X | X | X | X | X | 500,000 | | |
| | የኤጀንሲዉን የፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አቅም ማሳደግ | “” | X | X | X | X | X | | | |
| | የኤጀንሲዉን ዓላማ በተቀላጠፈ መልኩ ለማሳካት የሚያስችል የፊዚካል እና የካፒታል ስራ ዕቅድ ከስትራቴጂክ ዕቅድ ጋር አጣጥሞ ማዘጋጀት | የዕቅድና የበጀት ዝግጅት አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት | X | X | X | X | X | 200,000 | | |
| | የመደበኛ እና የፕሮጀክት ስራዎች አፈጻጸማቸዉ በወጣላቸዉ መመሪያ መሰረት እንዲዘጋጁ ማድረግ፣ | “” | X | X | X | X | X | | | |
| | በዕርዳታ የሚገኙ የፕሮጀክት ስራዎችን ማስተባበር | “” | X | X | X | X | X | | | |

| | | | የጊዜ ሰሌዳ | | | | | ለስራዉ የሚያስፈልገዉ | የፋይናንስ ምንጭ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ስትራቴጂክ ጉዳይ | መወሰድ የሚገባዉ እርምጃ | አስፈጻሚ አካል | 03 | 04 | 05 | 06 | 07 | የወጪ ግምት (በሺህ ብር) | ከመንግስት | ከእርዳታ |
| ኤጀንሲው ጤናማ እና ምቹ የሥራ አካባቢ ያለመኖር እና የኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታን ለመዋጋት በቁርጠኝነት ያለመነሳት | • በኤጀንሲዉ ምቹና ጤናማ የሥራ አካባቢን መፍጠር<br>• ኤጀንሲዉ የኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታን ለመዋጋት በቁርጠኝነት መነሳት | “” | | | | | | 300,000.00<br>300,000.00 | | |
| አድሎና መድሎ የሌለበት ግልጽነት የተሞላ የዉይይት ባህል በስራ አካባቢ ያለመዳበር | • አድሎና መድሎ የሌለበት ግልጽነት የተሞላ የዉይይት ባህል በስራ አካባቢ ማዳበር | “” | | | | | | 400,000.00 | | |
| ለኤጀንሲዉ የሴቶች በሁሉም መስክ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ አለመሆን | • በኤጀንሲዉ የሴቶች በሁሉም መስክ እኩል ተጠቃሚና ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ | | | | | | | 500,000.00 | | |
| | • በመንግስት የወጣዉን የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ ደንቦችና መመሪያዎች ከኤጀንሲዉ ተግባርና ሀላፊነት ጋር በማጣጣም ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማጥናት መቀየስና ተግባራዊነቱን መከታተል፣ | | | | | | | | | |

# 13. ክትትልና ግምገማ

የድርጅቱን የዓምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ በመተግበር ሂደት ውስጥ የዕቅዱን አፈፃፀም ውጤታማነትና በሂደት ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን በመለየት በወቅቱ የእርምት እርምጃ በመውሰድና ዕቅዱን ለማሳካት እንዲቻል የሚከተሉት የክትትልና የግምገማ ስልቶች ተቀይሷል፡፡

## 13.1 ክትትል

የስትራቴጂክ ዕቅዱን አፈፃፀም ለመከታተል እንዲቻል

1 ወርሀዊ፣ የየሩብ ዓመት፣ የስድስት ወር፣ የዘጠኝ ወርና ዓመታዊ ሪፖርት በሥራ ክፍሎች ማዘጋጀትና ማቅረብ፣

2 በመሥክ ጉብኝት ክትትል፣ የኤጀንሲው ሥራ በታቀደለት ጊዜና በሚፈለገው ሁኔታ መከናወን ስለመቻሉ በሩብ ዓመት ወይም መንፈቅ ዓመት የዴስክና የመስክ ክትትል በማድረግ በግንባር የማየት ሥርዓት በዋናው መ/ቤት፣ በቅርንጫፍ ፅ/ቤቶችና በጣቢያዎች ማከናወን፣

3 ውይይት፣ በዕቅድ ዘመኑ የሥራን ሂደት ለመከታተል ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱ በልዩ ልዩ የስራ ክፍሎች መካከል የሚደረግ ውይይት ሲሆን፤

ሀ. በዘርፍ ኃላፊዎችና ሠራተኞች መካከል በየወሩ፣

ለ. በአመራር አካላት መካከል በየወሩና በየሩብ ዓመቱ ማጠቃለያ የሚከናወን ውይይት የዕቅዱን አፈፃፀም ለመከታተል ያመቻሉ ተብለው የሚታሰቡ ስልቶች ናቸው፡፡

## 13.2 ግምገማ

በዕቅድ ዘመኑ ውስጥ እንዲከናወኑ የታቀዱ ሥራዎችን ውጤት ለማወቅና ለመገምገም እንዲቻል፤

1 የሥራ ውጤቶችን በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ፣ በየመንፈቀ ዓመቱ በየዘጠኝ ወሩና በዓመቱ የሚቀርቡ ሪፖርቶችን በመገምገም፣

2 እንደየሥራ ዘርፉ ባህርይ በሚሰጡ አገልግሎቶች ብቃት ላይ በሠራተኞችና በኃላፊዎች በባለድርሻዎችና በሥራ ዘርፎች መካከል በየሩብ ዓመቱ ወይም በየመንፈቅ ዓመቱ በውይይት የሥራ ውጤቶችን መገምገም፣

3 በተከናወኑ ሥራዎች ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች የተገኘ ለውጥን በተለያየ መንገድ (እንደ መጠይቅ፤ ውይይቶች ምልከታ ወዘተ. . . ) ለመገምገም፤ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ታቅዷል፣

4 በግምገማው ውጤት መሰረት ደካማ ጎናችንን ለመሻሻልና የበለጠ ለማጎልበት እርምጃ ሊወሰድ ታቅዷል፡፡

# 14 ታሳቢዎችና ስጋቶች

የስትራቴጂክ ዕቅዱን በመተግበር ሂደት ውስጥ የሚከተሉትን ታሳቢዎችና ስጋቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይገመታል..

## 14.1 ታሳቢዎች

**ለስትራቴጂክ ዕቅዱ አፈፃፀም፡-**

- የበላይ አመራር ቁርጠኝነት እንደሚኖር፣
- የመንግስት፣ የባለድርሻዎች፣ ተባባሪዎችና የለጋሽ ድርጅቶች ሙሉ ድጋፍ እንደሚገኝ፣
- የሠራተኞች የሥራ ተነሳሽነት እንደሚኖር፣

- የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄድ መስኩ በልዩ ልዩ ክፍለ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተገቢ ሚና መጫወት መቻልን፣

## 14.2 ስጋቶች

**በስትራቴጂክ ዕቅዱ አፈፃፀም ላይ፡-**

- ሊከሰቱና ቅድሚያ ሊሰጣቸው በሚችሉ ጉዳዮች ምክንያት ዕቅዱን ለማስፈፀም የሚያስችል በቂ በጀት ያለማግኘት፣
- ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎች አለመሟላት፣
- የለጋሽ አገሮች/ተቋማት የእርዳታ ፖሊሲ መለዋወጥና በዚህም ምክንያት ድጋፍ ማጣት፣
- ብቃትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች መፍለስ ፣
- የቴክኖሎጂ በፍጥነት መቀያየር የመሳሪያዎች ከአገልግሎት ውጪ መሆን የሚያስከትለው ጫና፣
- የጣቢያ መቋቋሚያ ቦታዎች በሚፈለጉ አካባቢዎች ማግኘት አለመቻል፣
- የመገናኛ ሬዲዮኖች ለመትከል የተገነቡ ቢሮዎች እጥረት፣
- የህብረተሰቡ የእምነትና የባህል ተፅዕኖ በሚታሰበው ደረጃ አለመቀየር፣

ስጋቶች አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል የሚል ግምት አለ፡፡